# አዲሰ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩሚቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፣ ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ- ምረቃ መርሐ-ግብር


# የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ በ2015 ዓ/ም አገልግሎት ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መጽሐፍ ምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብ ግምገማ

አማርኛን በማስተማር ኤም.ኤ ድግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ


ነጻነት ናኔቻ


ጥር 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብ ፍተሻ

# አዲሰ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ- ምሪቃ መርሐ-ግብር

አማርኛን በማስተማር ኤም.ኤ ድግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

በነፃነት ናኔቻ

ጥር 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

**አዲሰ አበባ ዩኒቨርስቲ**

**የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጋዜጠኝነትና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ፣ ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ- ምረቃ መርሐ-ግብር**


# የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብ ፍተሻ

አማርኛን በማስተማር ኤም.ኤ ድግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ


ነፃነት ናኔቻ



ጥር 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

**አማካሪ**

ማትሠው አስራቴ (ዶ/ር) ፊርማ ------------------------ -----------------

**ፈታኝ**

1 -------------------------------- ፊርማ -------- ------------------------------

2----------------------------------- ፊርማ-------- ------------------------------

## ምስጋና

በቅድሚያ አስጀምሮ ላስፈጸመኝ አምላኬ ቸሩ እግዚአብሔር ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡ በመቀጠልም ለዚህ ጥናት ማሳካት ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ስህተቶቼን በማረም ፤ የአሰራር መንገዶችን በማሣከት ክትትላቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ሙሉሰው አስራቴ (ዶ/ር) ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ጽሑፉን በመተየብ እና በማረም ከጎኔ ላገዘቸኝ ጓደኛዬ ሳራ ነጋሽ ከልብ አመሰግናለው፡፡ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ሚረጃዎችን በማስጠት ፣ መጠይቆችን በመሙላት ትብብር ያደረጉልኝን መምህራን አመሰግናለሁ፡፡ በአጠቃላይ ሀሳብ በማስጠት ፣ ስደክም በማበረታታት ከጎኔ የነበራችሁትን ሁሉ ቸሩ እግዚአብሔር የልባችሁን መሻት ይፈጽምላችሁ ፡፡

## ማውጫ

# Contents

ምስጋና ........................................................ v

ማውጫ........................................................ vi

አጠቃሎ ........................................................ x

ምዕራፍ አንድ ........................................................ 1

መግቢያ ........................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................ 3

የማዳመጥ ክሂል ዙሪያ የተነሱ ችግሮችን ለመቅረፍ በጥናትና ምርምር የተደገፈ መፍትሔ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ማሻ በማድረግ ጥናት እንድታካሔድ ያነሳሳት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡- .... 3

1. በመምህርነት በምታገለግልበት ወቅት በየአመቱ የምታገኛቸው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ተረጋግተው ለማዳመጥና ለተግባራት ምላሽ ለመስጠት ያላቸውፍላጎት በጣምዝቅተኛ መሆኑ ........................ 3

2. የአዳምጦሚረዳት ክሂል ለሚፈተሽ የሚሰጡ ተግባራትን እንዲሰሩ ሲጠየቁ የሚሰጧቸውምላሾች ክፍል ደረጃው ከሚጠበቀው በታች መሆኑ፡፡ ........................................ 3

3. የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ት/ት ምንቦችና ሚልመጃዎች አቀራረብ ፍተሻ በሚል ርዕስ በየደረጃው በመማኙ ት/ቤቶች ዙሪያ የአማርኛ አፈ ፈት፣ ኢ አፈ ፈትና የሁለቱም ጥምረት ተማሪዎች የተሰሩ ጥናቶች ውጤት ችግሮቹ እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ይህም ቀጣይ ጥናቶች እደሚያስፈልጉና ችግሮቹ እንዳልተቀረፉ የሚያመላክቱ በመሆናቸው ተከታታይነት ያለው ጥናት ያስፈልጋል ብላበማምኗ ነው፡ .................... 3

በርዕሱ ዙሪያ ጥናት ካደረጉት መካከል በምሳሌነት ........................ 3

1ኛ. ማስፍን ደፈረሱ (2000) የጥናቱ ውጤት እንደሚያመላክተው ሚልመጃዎቹ ከተተግባሪነት፣ ከቅደም ተከተል፣ ከተገኒነት ወዘተ… አንፃር የተሸሉ ሲሆኑ ከተሰጠው ጊዜ ከሳቢነትና ከሌሎች ክሂሎች ጋር ከማያያዝ አንፃር ጉድለት አለው፡ ........................................................ 3

አጥኚዋ ይህ ጥናት ቀደምት አጥኚዎች ባላተኮሩበት ተማሪዎች ላይ ተማስርቶ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ ምንባቦችና ሚልመጃዎችን ለሚፈተሸ ተነሳስታለች፡፡ በመሆኑም በቀደምት አጥኚዎች ያልተዳሰሱ ሌሎች ጉዳዮች ካሉ ሚፈተሽ፣ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች እንዴት ሊቀረፉ ይችላሉ ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ሚፈላለግ፤ የመፍትሔ ሀሳቦችን ማቅረብና ጥናቱ በሚከሄድበት ት/ቤትና በምታስተምራቸው ተማሪዎች ላይ ለውጥ ማምጣት ስለፈለገች በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናቷን ለማድረግ ተነሳስታለች፡፡ .................... 3

በዚህም ማሰረት ጥናቱ ለሚከተሉት ማሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለማስጠጥ ሞክሯል፡፡ ....................4

1. የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር በመማሀሩ መምሪያ የተዘጋጁ ምንባቦች አፈ ፈት ታሳቢ አድርጎ ለደረጃው በሚሞጥን መልኩ ቀርበዋል? ........................................4

2. የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የቀረቡ ምንባቦችና መልመጃዎች የቀረቡለትን ዓላማ ለማሳካት የሚችሉ ናቸው?..4

3. ለማዳመጥ ክሂል ለማስተማር የተዘጋጁ ምንባቦች አስፈላጊውን የማስተማሪያ መሳሪያ አካተዋል ወይ የሚሉ ናቸው፡ ..............................................4

1.3 የጥናቱ አላማ.........................................4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ......................................4

1.5 የጥናቱ ወሰን .......................................5

ምዕራፍ ሁለት ...........................................5

ክለሳ ድርሳናት .........................................5

2.1 የማዳመጥ ትምህርት ምንነት ...............................5

2.2 የማዳመጥ ትምህርት አላማዎች ..............................6

2.3 የማዳመጥ ደረጃዎች .....................................7

2.4 የማዳመጥ ክሂልን በክፍል ውስጥ አቀራረብ ስልቶች ...............8

2.4.1 ቅድመ ማዳመጥ ......................................8

2.4.2 ማዳመጥ ...........................................9

2.5.3 ድህረ ማዳመጥ ......................................9

2.5 የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ መሳሪያዎች .......................10

2.5.1 ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ...................................10

2.6.2 የተቀረጹ ስራዎች ....................................11

2.7.3 ቀጥተኛ ቃላዊ ገለጻዎች..................................11

2.8.4 ስዕል ካርታ ሰንጠረዥ መልክ...............................11

2.7 በማዳመጥ ትምህርት ጊዜ የመምህራን ተግባር ......................12

2.8 በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች አቀራረብ.............14

2.8.1 ቅድመ ማዳመጥ ......................................14

2.8.2 የማዳመጥ ጊዜ .......................................15

2.8.3 ድህረ ማዳመጥ ........................................ 15

2.9 የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ምንባቦች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦች ........ 16

2.9.1 ቋንቋ ........................................ 16

2.9.2 ርዝመት ........................................ 17

2.9.3 ይዘት ........................................ 17

2.9.4 በስዕል የታገዙ ምንባቦች ........................................ 18

2.9.5 ለትምህርት አሰጣጥ አመቺነት ........................................ 18

2.9.6 ለተማሪዎች ቅርበት ያላቸው ይዘቶች ........................................ 18

2.11 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........................................ 19

ምዕራፍ ሶስት ........................................ 21

የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ ........................................ 21

3.1 የጥናቱ ንድፍ ........................................ 21

3.2 የጥናቱ የሚረጃ ምንጮች ........................................ 21

3.3 የናሙና አመራረጥ ........................................ 22

3.3.1 የጥናቱ ክልል አመራረጥ ........................................ 22

3.3.2 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ........................................ 22

3.3.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........................................ 22

3.3.4 የመምህራን አመራረጥ ........................................ 22

3.4 ሚረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................................ 23

3.4.1 የሰነድ ፍተሻ ........................................ 23

3.4.2 የጽሑፍ ማጠይቅ ........................................ 23

3.4.3 ምልከታ ........................................ 23

3.5 የሚረጃ አተናተን ዘዴ ........................................ 24

ምዕራፍ አራት ........................................ 25

የሚረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ ........................................ 25

4.1 መግቢያ ........................................ 25

4.2 አዳምጦ ሚረዳት ምንባቦች ግምገማ ........................................ 25

4.2.1 አዳዲስ ሚጃዎችን ስለሚያዛቸውና በስፋት የመቅረብ ሁኔታ ........................25

4.2.2 ስነ-ጽሁፋዊ ይዘቶችን የማከተታቸው ሁኔታ ................................28

4. ቋንቋ እና ይዘት ..............................................29

4.2.4 ከተማሪዎች የእለት ከእለት ገጠመኝ ጋር ያላቸው ቅርበት ....................31

4.2.5 ስዕላዊ መግለጫ ስለሚያዛቸው........................................33

4.3 የመልመጃዎች የትምህርቱን አላማ የማሳካት ብቃት ...............................34

4.4 ምንባቦችና መልመጃዎች ክህሎቱን ለማስተማር ያላቸው አመቺነት .....................39

4.5 ከምልከታ የተገኙ ምላሾች ትንተና .....................................40

4.5.1መምህራን የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ያላቸው ተነሳሽነት .....................40

4.5.2 የመምህራን የማዳመጥ ትምህርት አቀራረብ................................44

4.5.3 ተማሪዎች ለምንባቦችና መልመጃዎች የሚሰጡት ትኩረት .......................47

ምዕራፍ አምስት ...................................................49

ማጠቃለያ እና አስተያየት ..............................................49

5.2 አስተያየት ....................................................50

ዋቢዎች ........................................................52

አባሪዎች .......................................................55

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ይዘት የተነሳው አቢይ አላማ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ የ8ኛክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብን ሚፈተሸ ነው፡ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ አጥኚዋ በዋነኛነት አይነታዊ ምርምር የተጠቀመች ሲሆን በደጋፊነት ደግሞ መጠናዊ ምርምርን ተጠቅማለች፡፡ የመረጃ ማሰብሰቢያ ማሳሪያዎች የሰነድ ፍተሻ ፣ በመምህራን የተሞሉ የጽሁፍ መጠይቆች እና የክፍል ምልከታ ናቸው፡ ከመረጃ ምንጮች የተገኘው መረጃ በአግባቡ ተደራጅተው ትንተና ተደርጎባቸዋል ፡፡ለጥናቱ አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመከተል የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍት የተመረጡ ሲሆን፤ በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ 12 መምህራን የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ፤እንዲሁም ስድስት መምህራን ክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የክፍል ምልከታ ተደርጓል፡፡ ከመረጃዎቹ የተገኙት ውጤቶች የሚያመላክቱት ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች ከተማሪዎች የዕለት ገጠመኝ ጋር ያላቸው ግንኙነት አነስተኛ መሆኑ እንዲሁም በቅድመ ማዳመጥ በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ጥያቄዎች የቀረቡበትን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሆነው አለመቅረባቸውን ፣ ለማስተማሪያነት የቀረቡት ምንባቦች አስፈላጊ የማስተማሪያ ማሳሪያ አለማካተታቸውን ፣ ስለዚህም እነዚህን የጥናት ውጤቶችን ማሰረት በማድረግ ለወደፊቱ አሻሽሎ ለማቅረብ የሚያስችሉ አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አራቱን የቋንቋ ትምህርት ክህሎቶች ይይዛል ፡፡ ከክህሎቶች ውስጥ አንዱ የማዳመጥ ክሂል ነው፡ ሚረው (1998 ፤ 171) እንደገለጹት ማዳመጥ ከጠዋት እስከ ማታ ፤ ከአመት እስከ አመት ፤እድሜ ልኩን የሰው ልጅ የሚተገብረው ተግባር ነው፡ማዳመጥ በእለት ከእለት ህይወታችን ውስጥ ከማንኛውም ክሂል ይበልጥ በስፋት ያገለግላል፡፡የማዳመጥ ክሂል ትምህርት እስከ 1980ዎቹ ድረስ አስፈላጊነቱ ሳይታመንበት የቆየ ክሂል መሆኑን ያስገነዝባሉ ፡፡ ትኩረት ያልተሰጠበትን ምክንያትም እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

1 መምህራን የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በምን አይነት መንገድ ቢቀርብ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል በእርግጠኝነት ባለማወቃቸው ፤

2 መምህራን የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በተፈጥሮ የሚዳብር ነው ብለው ስለሚያምኑ ለትምህርቱ ትኩረት ባለማስጠታቸው ነው፡

ምንም እንኳን የማዳመጥ ክሂል ትምህርት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ትኩረት ባይሰጠውም በርካታ ጥቅሞች አሉት ፡፡ ይህን አስመልክቶ Underwood (1994፤23) ሲገልጹ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበት እና ትኩረት ተሰጥቶት መቅረብ ይገባዋል፡፡ የማዳመጥ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት መቅረቡ ተማሪዎች ቃላትንና የተለያዩ ድምጾችን ከማለየት አንስተው እስከ ተያያዥነት ያላቸው ንግግሮችን ሚረዳት ለማስቻል ፤በንግግር ወቅት በተናጋሪው በኩል የሚሰሙ የተለያዩ ድምጾችን ለማንዘብና ሚልእክታቸውን ለሚረዳት ፤ በንግግርና በትምህርታዊ ንግግር መካከል ያለውን ልዩነት እንዲገነዘቡ ለማስቻልና ለማሰሉት ይጠቅሚል፡፡ እንዲሁም Grant (1989 ፤ 19) የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ለማሳደግ እና ተማሪዎች ትምህርታቸውን በቀላሉ ማከታተል እንዲችሉ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ያስረዳሉ፡፡

ስለሆነም የማዳመጥ ክሂል ትምህርትን የተሳካና ውጤታማ ለማድረግ መምህሩ የማዳመጥ ትምህርት እንዴት ማካናወን እንዳለበት ማወቅና ማጠቀም ማቻል ይጠበቅበታል ፡፡ምክንያቱም መምህሩ በሚያስተምርበት ወቅት ተገቢዉን የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ስልት አለማከተሉ የሚያስከትለው ተጽእኖ ከፍተኛ ነው ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አዳምጦ የሚረዳት ክሂል መልመጃዎች እንዴት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሊዘጋጁ እንደሚችሉ McDonough (1994) ሲያብራሩ የማዳመጥ ክሂልን የሚያዳብሩ መልመጃዎች በእውነት ሐሰት፣ በአዛምድ ፣ ባዶ ቦታዎችን በመሙላት … መልኩ ሊቀርቡ ይችላሉ ፡፡ እንደ McDonough (1994) ገለጻ የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚያስችሉ መልመጃዎች ሲዘጋጁ የሚከተሉት ነጥቦች ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል ፡፡ አጠር ያሉ ምንባቦችን ማዘጋጀት ፣ ተማሪዎች ከርእሱ ተነስተው በርእሱ ዙሪያ ምን አይነት ሐሳብ ሊነሳ እንደሚችል እንዲገነዘቡ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ፣ እያዳመጡ መማሪያዎችን እንዲከተሉ የሚያስችሉ መልመጃዎች ፣ የተለየዩ ፎቶግራችን በማጠቀም የሚያዳምጡትን ነገር ከሚያዩት ጋር እንዲያዛምዱ የሚያደርጉ መልመጃዎች ፣ የሰዎችን ቃለ ምልልስ የሚያዳምጡበትን ሁኔታ የሚያመቻቹ መልመጃዎችን ማዘጋጀት፡፡እነዚህ ነጥቦች በአንድ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ መልመጃዎች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊሰጥባቸው እንደሚገባ ምሁሩ ያብራራሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተነሱት ነጥቦች እንደሚጠቁሙት የማዳመጥ ትምህርት በጣም አስፈላጊ ክሀሂል ነው ፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ርእስ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ እታገኝ( 1986) ማስፍን(2000) ቶማስ(2000) እንዲሁም አልማዝ(2006) ጥናት ያካሄዱ ሲሆን እነሱ ያጠኑት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በአተገባበር በክፍል ደረጃ እንዲሁም በቦታ የተለያዩ ናቸው ይህን በማንዘብ አጥኝዋ በክሒሉ ማዳበር ላይ የራስዋን አስተዋጽዎ ለማበርከት በመማሪያ መጻሕፍት የሚቀርቡ ምንባቦችና ከምንባቦቹ የሚወጡ መልመጃዎች አቀራረብ ትኩረት ተሰጥቶት ቀርቧል? ወይስ አልቀረበም? የሚለውን የ8ኛ ክፍል መማሪያ እና ማስተማሪያ መጽሐፍን ተተኳሪ በማድረግ ይህ ጥናት ቀርቧል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የማዳመጥ ክሂል ዙሪያ የተነሱ ችግሮችን ለመቅረፍ በጥናትና ምርምር የተደገፈ መፍትሔ ያስፈልጋል፡፡ 1በመሆኑም አጥኚዋ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ማ ሻ በማድረግ ጥናት እንድታካሂድ ያነሳሳት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው -

1 በመምህርነት በምታገለግልበት ወቅት በየአመቱ የምታገኛቸው አብዛኞዎቹ ተማሪዎች ተረጋግተው ለማዳመጥና ለተግባራት ምላሽ ለመስጠት ያላቸውፍላጎት በጣምዝቅተኛ መሆኑ

2. የአዳምጦመረዳት ክሂል ለሚፈተሽ የሚሰጡ ተግባራትን እንዲሰሩ ሲጠየቁ የሚሰጧቸውምላሾች ክፍል ደረጃው ከሚጠበቀው በታች መሆኑ፡፡

3. የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ት/ት ምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብ ፍተሻ በሚል ርዕስ በየደረጃው በሚገኙ ት/ቤቶች ዙሪያ የአማርኛ አፈ ፈት፣ ኢ አፈ ፈትና የሁለቱም ጥምረት ተማሪዎች የተሰሩ ጥናቶች ውጤት ችግሮቹ እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ይህም ቀጣይ ጥናቶች እደሚያስፈልጉና ችግሮቹ እንዳልተቀረፉ የሚያመለክቱ በመሆናቸው ተከታታይነት ያለው ጥናት ያስፈልጋል ብላበማመኗ ነው፡

በርዕሱ ዙሪያ ጥናት ካደረጉት መካከል በምሳሌነት

1ኛ. ማስፍን ደፈረሱ (2000) የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው መልመጃዎቹ ከተተግባሪነት፣ ከቅደም ተከተል፣ ከተገኒነት ወዘተ… አንፃር የተሸሉ ሲሆኑ ከተሰጠው ጊዜ ከሳቢነትና ከሌሎች ክሂሎች ጋር ከማያያዝ አንፃር ጉድለት አለው፡

አጥኚዋ ይህ ጥናት ቀደምት አጥኚዎች ባላተኮሩበት ላይ ተመስርቶ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ ምንባቦችና መልመጃዎችን ለመገምገም ተነሳስታለች፡፡ በመሆኑም በቀደምት አጥኚዎች ያልተዳሰሱ ሌሎች ጉዳዮች ካሉ ሚፈተሸ፣ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች እንዴት ሊቀረፉ ይችላሉ ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ሚፈለለግ፤ የመፍትሔ ሀሳቦችን ማቅረብና ጥናቱ በሚካሄድበት ት/ቤትና በምታስተምራቸው ተማሪዎች ላይ ለውጥ ለማምጣት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናቷን ለማድረግ ተነሳስታለች፡፡

በዚህም መሰረት ጥናቱ ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለማስጠጥ ሞክሯል፡፡

1. የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር በመምህሩ መምሪያ የተዘጋጁ ምንባቦች አፈ ፈት ታሳቢ አድርጎ ለደረጃው በሚመጥን መልኩ ቀርበዋል?

2. የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የቀረቡ ምንባቦችና መልመጃዎች የቀረቡለትን ዓላማ ለማሳካት የሚችሉ ናቸው?

3. ለማዳመጥ ክሂል ለማስተማር የተዘጋጁ ምንባቦች አስፈላጊውን የማስተማሪያ መሳሪያ አካተዋል ወይ የሚሉ ናቸው።

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዓብይ አላማ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብ ሚፈተሽ ነው። ከዚህ ዓብይ አላማ ስርም የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች ተነድፈዋል፡

- የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር በመምህሩ መምሪያ የተዘጋጁት ምንባቦች ተገቢ ትኩረት ተሰጥቷቸው ከመቅረባቸው አንጻር ይገመግማል፡፡
- የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች እና መልመጃዎች የቀረቡበትን አላማ ለማሳካት የሚችሉ መሆናቸውን ይመረምራል፡፡
- የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች ተገቢውን የማስተማሪያ መሳሪያዎችን አካተዋል? የሚለውን ይመረምራል ፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡ -

. የጥናቱ ዉጤት መነ ሻ በማድረግ የመጻሕፍት አዘጋጆች ለክፍል ደረጃዉ ተስማሚ የሆኑና የማዳመጥ ኪሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ ምንባቦች እና መልመጃዎችን ለማዘገጀት ሐሳብ ያገኙበታል፡፡

. መምህራን የሚደመጥ ኪሂል ምንባቦችን እና መልመጃዎችን ለተማሪዎቻቸዉ በሚያቀርቡበት ጊዜ በተሸለ የአቀራረብ ስልት ለማቅረብ ሚረጃ የገኛሉ ፡፡

. በርዕሱ ዙሪያ ሰፊ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች መነሻ ሀሳብ በመሆን ያገለግላል ፡፡ .

## 1.5 የጥናቱ ወሰን .

ይህ ጥናት ዋነኛዉ አላማ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ የስምንተኛ ክፍል የአማሪኛ ቋንቋ ትምህርት ምንባቦች እና ጫላመጃዎች አቀራረብ ሚፈተሸ እነደሚሆኑ በየ እለቱ የመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ዉስጥ የሚደመጥ ኪሂልን መሠረት አድርገዉ የቀረቡ ምንባቦች እና ጫላመጃዎች ሚፈተሸ ነዉ ፡፡ ይህ ጥናት ከማዳመጥ ክሂል ዉጪ በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ላይ አለማተኮሩ አንዱ ዉስንነት ነዉ ፡፡ ከዚህም ሌላ ጥናቱ የደረሰበት መደምደሚያም ሆነ የመፍትሄ ሀሳብ የሚመለከተዉ ተጠኚ የሆኑትን የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን እና የስምንተኛ ክፍል የአማሪኛ ቋንቋ መማሪያ እና ማስተማሪያ መጽሐፍ ብቻ ነዉ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የማዳመጥ ትምህርት ምንነት

ማዳመጥ ከተናጋሪ አንደበት ወይም ከአንድ ከሚደመጥ ነገር የሚወጣ ድምጽን በአግባቡ መገንዘብ መቻል እንደሆነ Underwood (1989) ይገልጻሉ ፡፡ ማዳመጥ በተለያዩ ቦታዎችና አዉዶች ሊከናወን የሚችል ክሂል ነው ፡፡ ይህ ክሂል እንደ ማንበብና መጻፍ የግድ ትምህርት ቤት ገብቶ መማርን ላይጠይቅ ይችላል ፤ ነገር ግን እንደ Rixon(1990) አገላለጽ በመማር ልናዳብረው እንችላለን ፡፡የማዳመጥ ትምህርት የተማሪዎችን ተሳትፎ ያላካተተ እንደሆነና ተማሪዎች መምህሩ የሚሉትን ወይም በመቅረጸ ድምጽ ላይ የተቀረጸውን አዳምጠው ደብተራቸው ላይ በማስፈር ብቻ የሚያካብቱት ክህሎት እንደሆነ ተደርጎ ለብዙ ጊዜ ሲሰራበት እንደቆየ Anderson and LYnch ( 1988} ገልጸዋል፡፡ ይህን ሀሳብ Rixon(1990,1) ሲያጠናክሩት ‹‹የማዳመጥ ክሂል በማህበራዊ ህይወትና ልምድ የሚገኝ ስለሆነ ትምህርት አያስፈልገውም ››ብለው የሚያምኑ ጥቂቶች እንዳልነበሩ ጠቁመዋል፡፡

ማዳመጥ የሚአክት ወደ ጆሮ መድረስ ሳይሆን የደረሰውን ሚአክት መረዳትና መተርጎምን የሚያካትት ነው ፡፡ ስለዚህ ተማሪውን ስለማዳመጥ የምናስተምረው የሚያዳምጠውን እንዲያደራጀው ፣ እንዲረዳው ፣ እንዲተረጉመውና ምላሽ እንዲሰጥ በጥቅሉ በሀሳብ ልውውጡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ ነው ፡፡ የማዳመጥ ትምህርት የሚባለው ተማሪዎችን በዚህ ሚክ የማዳመጥ ክሂል ለማለማመድ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት ተግባር ነው (Underwood ፣1989) ፡፡

Littlewood (1981) በበኩላቸው <<የማዳመጥ ትምህርት ተማሪው በማዳመጥ ሂደት ውስጥ ጠንካራ ተሳታፊ የማድረግ ሂደት ነው፡ ይህም ማለት መዋቅራዊና ማህበራዊ የሆነውን አጠቃቀም እንዲለይ ማድረግ ነው>> በማለት ይገልጻሉ፡፡ ጥሩ አድማጭ የሚባለውን በተሟላ መንገድ ለማዳመጥ እንዲረዳው ተናጋሪውን ይጠይቃል ፡፡ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ተለምዷዊውን ማዳመጥ የመማር መንገድ በትምህርት ማዳበር አስፈላጊ የሚሆንባቸው ምክንያቶች ውስጥ ለአብነት ያህል ፣ አብዛኛውን ጊዜያችንን የምንሳልፈው በማዳመጥ በመሆኑ ፣ የዳበረ የማዳመጥ ችሎታ ሌሎችን ክሂሎች ለማዳበር የሚያግዝ መሆኑና ተማሪዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ማዳመጥን በትምህርት ቤት መማር ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው እሙን ነው፡ ይሁን እንጂ እንደ በርካታ የዘርፉ ምሁራን እምነት የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ተገቢ ትኩረት የተሰጠው አይደለም ፡፡ Karl (1996፣32) <<በበርካታ ሀገሮች አዳምጦ መረዳት የተማሪዎች ችግር ነው >> በማለት የገለጹ ሲሆን Ur (1984፣9) በበኩላቸው የክፍል ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት የአፈጻጸም ሂደትን በተማከተ በሚከተለው መንገድ ያብራራሉ፡ <<የክፍል ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት ክንውኖች ተፈጥሯዊዉን የማዳመጥ ተግባራት የሚያሟሉ ናቸው ፡፡የማስተማሪያ መጽሐፍ ይዘቶችም ከተለያዩ መጻህፍትና ጽሁፎች የተለቃቀሙ ተማሪው ለምን እንደሚያዳምጥም ሆነ ፣ምን እንደሚፈልግ ሳያውቅ የሚያዳምጣቸው ናቸው >> ፡፡

እንደ Underwood (1989፣1) አማላካከትም ቀደም ባሉት ጊዜያት የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የሚያስፈልግ ተደርጎ አይቆጠርም ነበር፡፡ማስተማር ማለት የመማር ሂደትን መደገፍ ነው ብለን ከተረዳንና የመምህሩን ሚና እንደረዳትነት ከወሰድነው የማዳመጥ ትምህርት አስፈላጊነት እንረዳለን ይላሉ፡፡ በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ እንደሚቻለው የማዳመጥ ትምህርት የዕለት ተዕለት ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በተግባቦት ጊዜ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች የበለጠ የምንጠቀምበት ስለሆነ የማዳመጥ ትምህርትን በክፍል ውስጥ መተግበር አስፈላጊ ነው፡

## 2.2 የማዳመጥ ትምህርት አላማዎች

የማዳመጥ ትምህርት የሚሰጥበት ዋና አላማ የተማሪዎችን ሚአክት የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ፣ ከተለያዩ የማዳመጥ ባህሪያት ጋር ለማስተዋወቅ ፣ ንግግርን ለማድነቅና ለማሳሰት እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ ፡፡

በድሉ (1996) የማዳመጥ ትምህርት አላማዎች እውቀትንና ሚረጃዎችን ለማግኘት ፣ መመሪዎችን ለማከተል ፣ ሚረጃን ለመተርጎምና ለማናዘብ ፣ የተነገረውን ነገር ለመመርመር ፣ ተናጋሪው የሚያስተላልፈውን ሐሳብና ዝንባሌ ለማየት ፣ ጭብጥና ደጋፊ ሀሳቦችን ማየትን ትኩረታቸው እንደሚያደርጉ ያስረዳሉ፡፡ Grant (1987 ፣19-20) መምህራን በማዳመጥ ትምህርት ጊዜ ትኩረት ሚድረግ ያለባቸውን አላማዎች እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ ድምጽን ማየትና ሚረዳት ፣ ቃላትን ለይቶ ማወቅ ፣ ትርጉምን ሚረዳት ፣ ሚረጃዎችን በአእምሮ ማያዝ ፣የአነጋገር ዘዬን ማየት ፣ የተላለፈን ሜልእክት አውድን ማነረት አድርጎ ሚረዳት፡፡እንዲሁም Underwood (1989 ፣4) እና Rixon (1986 ፣ 65) የክፍል ውስጥ አላማዎችን እንደሚከተለው ያብራራሉ ፡፡

- ተማሪዎች የማዳመጥ ልምድ እንዲኖራቸው ለማድረግ ፣
- ተማሪዎች የሚያዳምጡትን ነገር ፍሬ ሐሳብ እንዲጨብጡ ለማስቻል ፣
- ተማሪዎች በማዳመጥ ያገኙትን ሚረጃ ለሌላ ሰው በትክክል ማስተላለፍ እንዲችሉ ለማለማመድ
- ፣ ተማሪዎች ባዳመጡት ፍሬ ሐሳብ ላይ ተማስርተው በውይይት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግና
- በገሀዱ አለም በማዳመጥ መግባባትን በተሳካ ሁኔታ እንዲተገብሩ ለማስቻል ነው፡

## 2.3 የማዳመጥ ደረጃዎች

እንደ Nunan (2001 ፡23) አገላለጽ ማዳመጥ በስድስት ደረጃዎች ላይ የሚማነረት ሂደት እንደሆነና እነዚህን የማዳመጥ ሂደቶች ብናልፍ የተሻለ የማዳመጥ ሂደት እንደሚኖረን ይገልጻሉ ፡፡ እነዚህ ደረጃዎችም የሚከተሉት ናቸው ፡-

1 ማነማት ፡- በጆሯችን ውስጥ የገባው የንግግር ድምጽ ትርጉም የሚያገኝበት ሂደት ነው፡፡
2 ትኩረት ፡- በዚህ ሂደት ስናዳምጥ ትኩረት የተደረገባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች እየለየን መሆን አለበት፡፡
3 መገንዘብ ፡- በዚህ ሂደት ከሚደመጠው ነገር የሚገኘውን ሜልእክት እንዳለና የንግግሩን ጭብጥ ማናዘብና ሚረዳት ያስፈልጋል ፡፡
4 ማስታወስ ፡- ይህ የማዳመጥ ሂደት ግላዊ የማስታወስ ችሎታን የሚጠይቅ ፣ሜልዕክት መቀበያና ፍቺ ማገኛ ስለሆነ ከሌሎቹ የማዳመጥ ደረጃዎች የበለጠ ትኩረት ይፈልጋል፡፡
5 ማመዛዘን ፡- ይህ የማዳመጥ ሂደት የሚደመጠውን ነገር ከራስ ህይወትና አውድ ጋር እያዋሀዱ እና እያመዛዘኑ ማዳመጥ ላይ ያተኩራል ፡፡
6 ግብረ ሜልስ ፡- ያዳመጥነውን ነገር ሚረዳታችንን የምንገልጽበት ሂደት ነው፡፡

## 2.4 የማዳመጥ ክሂልን በክፍል ውስጥ አቀራረብ ስልቶች

የማዳመጥ ክሂል በክፍል ውስጥ ሲተገበር ሶስት ደረጃዎችን ይከተላል (በድሉ ፣1996 ፣ Rixon, 1986, underwood, 1989}

### 2.4.1 ቅድመ ማዳመጥ

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከሚቀርበው ንግግር ወይም ጽሁፍ ጋር ትውውቅ የሚያደርጉበት ነው ፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት ማሳረት በማድረግ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ስለሚደመጠው ነገር እንዲገምቱ የሚደረግበት ደረጃ ነው ፡፡ የቅድመ ማዳመጥ ክንውኖች ተማሪዎች ስለሚያዳምጡት ጉዳይ መረጃ የሚያገኙባቸው ናቸው ፡፡ምክንያቱም በተፈጥሮአዊ የማዳመጥ ሂደት ሰዎች ስለሚያዳምጡት ጎዳይ በቂ ግንዛቤ ሳይኖራቸው መልዕክቱን በሚገባ ሊረዱት አይችሉም ፡፡ሆኖም ግን አንድ አንድ መምህራን ተፈጥሮአዊ ከሆነው የማዳመጥ ትምህርት ውጪ ወደ መማሪያ ክፍል እንደገቡ ቴፕ በማከፈት ወይም በቀጥታ ምንባቡን በማንበብ ተማሪዎች እንዲያዳምጡ እና ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መንገድ መምህራን ሲያስተምሩ ምንም እንኳን ቃላቶቹ ለተማሪዎች አዳዲስ በይሆኑባቸውም መልዕክቱን ለሚረዳት የሚያስችል በቂ ዳራዊ እውቀት በጉዳዩ ዙሪያ ስለሚይኖራቸው የሚያዳምጡትን ጉዳይ በቀላሉ ሊረዱት እንደሚይችሉ (Underwood, 1989) ያስረዳሉ፡

እንደ Haozhang (1997፣33) አገላለጽ በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ የሚከናወኑ ጉዳዮች ተማሪው ስለ ሠርእሱ በቂ መረጃ እንዲያገኝና የቀደመ እውቀቱን ከቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ጋር እንዲያጣጥም ለማድረግ የሚያነሳሱ ናቸው፡

ከዚህም ሌላ አንድ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎች እንዲነቃቁ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ መምህራን የሚደመጠውን ነገር ከማቅረባቸው በፊት ተማሪዎች በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ፍላጎት እንዲያድርባቸው እና ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን የተለያዩ ስዕሎችን ፣ ፖስተሮችን ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎችን ማነሳሳት እንደሚኖርባቸው Rixon (1986፣1)ይገልጻሉ፡፡ ምሁሩ እንደሚገልጹት በቅድመ ማዳመጥ ደረጃ መምህራን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርባቸዋል ፡፡

- የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሳት ተማሪዎች የማነቃቃት ስሜት እንዲፈጥሩ ማድረግ ፤
- ተማሪዎች ከማዳመጣቸው በፊት ስዕሎችን እንዲመለከቱና እያዳመጡ ስለስእሎቹ ምንነት መግለጫ እንዲሰጡ ማድረግ ፤
- ከትምህርቱ ርዕስ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን መመዘን ፤
- ተማሪዎች በትምህርት ርእስ ዙሪያ ይነገራል ብለው የሚጠብቁትን ነገር በመጠየቅ እንዲገምቱ ማድረግ ፤
- ከትምህርቱ ርዕስ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን መመዘን

- ለትምህርቱ የቀረበውን ይዘት በተገቢው ሁኔታ እንዲረዱ የአዳዲስ ቃላት ፍቺን ለተማሪዎች ማሳወቅ ፤
- ከሚደመጠው የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ፣መረጃ ማሳሪያዎችን በማቅረብ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ ፤
- በማዳመጥ ጊዜ ሊሰሯቸው የሚችሉ ጥያቄዎችን ፣ በማዳመጥ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት እንዴት ማሰራት እንዳለባቸው አጠር ያለ ማብራሪያ ማስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.4.2 ማዳመጥ

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የሚደመጠውን ርዕሰ ጉዳይ በጥልቀት የሚያዳምጡበትና ተፈላጊ መረጃዎችን የሚያሰባስቡበት ነው፡ በመሆኑም ተማሪዎች የሚደመጠውን ጽሁፍ ወይም ንግግር በተማስጦ በማከታተልና ማስታወሻ በማያዝ ልምምዱን በተገቢ ሁኔታ እንዲያካሂዱ የሚደረግበት ነው፡ በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

> ተማሪዎች ስዕሎችን በትክክለኛ ቅደም ተከተላቸው እንዲያስቀምጡ ፤ ያልተሟሉ መረጃዎችንና እቅዶችን እንዲያሟሉ ፤አንድን ጽሁፍ ንግግር እያዳመጡ እያለ ቀጥሎ ምን ሊመጣ እንደሚችል እንዲገምቱ ፣ የሚነገረውን ነገር በቅደም ተከተል ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ ፣ አያያዥ ቃላትን ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ ማድረግ ይገባቸዋል ፤ ምክንያቱም እንደነዚህ ያሉ ቃላት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሀሳቦች መካከል ያለውን የእርስ በእርስ ዝምድና ስለሚገልጹ ነው (በድሉ፤1996) ፡፡

በማዳመጥ ሂደት ወቅት በየመሀሉ ምንባብን ገታ እያደረጉ ቀጥሎ ሊከተል የሚችለውን ሀሳብ ማስገመትና ምንባቡን ሁለት ጊዜ ማስደመጥ ተገቢ እንደሆነ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ የማዳመጥ ትምህርት ተማሪዎቹ የቋንቋውን የድምጽ አወጣጥ ፣ንበት መረዳት እንዲችሉና ቋንቋውን ለንግግር ተግባቦት በሚጠቀሙበት ጊዜ ትክክለኛውን የቋንቋ አጠቃቀም እንዲገለገሉበት ለማድረግ ወሳኝ ሚና ስለሚጫወት የሚደመጠውን ነገር ሲያቀርብ ግልጽና ትክክለኛ በሆነ መንገድስ መቅረብ ይጠበቅበታል (Underwood ፡1989)፡፡በመጨረሻም ተማሪዎቹ ሚደመጃዎቹን ሰርተው እንደጨረሱ መምህሩ ወዲያው ግብረ መልስ ማስጠት ይኖርበታል፡፡ ይህም ተማሪዎቹን ምን ያህል ስኬታማ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ ለመረዳት እንደሚጠቅም Underwood (1989፣73) ገልጸዋል፡፡

## 2.5.3 ድህረ ማዳመጥ

ተማሪዎች ያዳመጡትን ንግግር ወይም ጽሁፍ ማስረት በማድረግ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ምላስ የሚሰጡበት ክፍል ነው ፡፡ በዚህ ክፍል ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን ከዳመጡት መረጃ ጋር በማቀናጀት የማዳመጥ ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት ክፍል ነው (Rixon, 1986) ፡፡ በዚህ ተግባር ጊዜ ተማሪዎች ማግኘት

ያለባቸውን መረጃ በትክክል ማግኘታቸውን ያረጋግጡበታል ፣ የትምህርት ይዘቱን በጥልቀት በመመርመር የተናጋሪዎችን ዝንባሌ ለማወቅ ይሞክሩበታል ፣ መምህሩ በሚሰጠው ግብረ መልስ በግል ፣በጥንድ ፣በቡድን ሆነው ለሰጡት መልሶች እንዲያማክሩ ይደረግበታል ፣ ባዳመጡት ጽሁፍ ውስጥ የተሰማቸውን እንዲናገሩ ይደረግበታል በማለት በድሉ(1996፣ 49) እና Underwood (1989፣ 45) ገልጸዋል፡፡

## 2.5 የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ መሳሪያዎች

Underwood (1989) እንደገለጹት የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ የተለያዩ ማስተማሪያ መሳሪያዎች አሉ ፡፡ ማዳመጥን የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተብለው በምሁሩ ከተገለጹት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡

### 2.5.1 ሥነ-ጽሁፋዊ ስራዎች

ከማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ውስጥ አንዱ ስነጽሑፋዊ ስራዎች ናቸው ፡፡ በስነጽሁፋዊ ስራዎች ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎች በእውነተኛ አውድ ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ አገባቦችን እንዲያጡኑ ፣ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን በእውነተኛ አውዳቸው እንዲያገኙ ፣ የአማላካከት መገለጫን እንዲለኩ እና ተጨበጭ በሆነው የሰዎች ህይወት አውድነት ቋንቋን እንዲማሩ ያስችላል በድሉ (1996፣ 3-4)፡፡ እንደ ምሁሩ አገላለጽ ስነ-ጽሁፍ በባህሪው ውጨዊ ግፊትን ሳይፈልግ ተማሪው በራሱ ተነሳሽነት የሚያዳምጥበትን ሁኔታ የሚያመቻች በመሆኑ ክሂሉን ለማስተማር ተመራጭነቱን የጎላ ያደርገዋል ፡፡

Hamar (2001፣ 213) እንደገለጹት ለተማሪዎች አጫጭር ታሪኮችን (ልብወለዶችን) በክፍል ውስጥ በማቅረብ የማዳመጥ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ይቻላል ፡፡ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ስራዎችን ለማስተማሪያነት ስንመርጥ ተማሪዎች በሚበብላቸው የስነጽሁፍ ስራ ውስጥ ያሉትን ገጸባህሪያት ይለያሉ፣ የተሰማቸውን አስተያየት ይሰጣሉ ፣ እያዳመጡ ማስታወሻ በመያዝ ታሪኩ ወዴት እንደሄደና ፍጻሜው ምን ሊሆን እንደሚችል ይተነብያሉ፡፡ Andersoon and Lynch (1991) ይህን ሀሳብ በመደገፍ ማዳመጥን ለማስተማር በሚያመች መልኩ አጫጭር ጽሁፎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቢቀርቡ መልካም እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ Bireen (1976) ከዚህ ጋር በተያያዘ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ሳቢነት ስላላቸው ለክሂሉ መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ፡፡የትምህርት አሰጣጡም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድን በቡድን በማድረግ የተለያዩ ተውኔቶችን ጭውውቶችን እንዲለማመዱ በማድረግ የማዳመጥ ክሂልን ማስተማር ይቻላል ፡፡ Cuningworth (1989 ፣43 ) እንደገለጹትም አጫጭር ነገር ግን ሳቢነት ያላቸው አንቀጾችን ለተማሪዎች በማንበብ የሰሙትን በደንብ መገንዘባቸውን እና አለመገንዘባቸውን ለማጠየቅ አመቺ ሊሆኑ ስለሚችሉ ቢመረጡ መልካም ነው ፡፡

Collie and Stephen (1987) እንደሚያብራሩት ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ማዳመጥን ለማስተማር ቢመረጡ የጎላ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ፡፡ዋናው ነገር ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ውስጥ መልመጃዎች ሲዘጋጁ

ተማሪዎች በተሰጣቸው ጊዜ አድምጠው እንዲሜልሷቸው በሚያስችል ሜልኩ መሆን አለበት፡፡ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች እንደምንገነዘበው ስነጽሁፋዊ ስራዎች የተለያዩ ማህበራዊ አውዶችን ማረት አድርገው ስለሚዘጋጁ እና ሳቢነት ስላላቸው በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በማካተት የማዳመጥ ክሂልን የመማር ማስተማር የተሻለ ማድረግ ይቻላል ፡፡

## 2.6.2 የተቀረጹ ስራዎች

የተቀረጹ ስራዎችን ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎችን ማዳመጥን ማስተማር ይቻላል፡፡በተለያየ ወቅት የተካሄዱ ስብሰባዎችን የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች የሚያሳሉትን ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎች እያዳመጡ ማን ምን እንዳለ ፣ እንዴት እንደተገለጸ በምን ሁኔታ ውስጥ እንደተነገረ እንዲሜልሱ ቢደረግ ውጤታማ የሆነ የማድመጥን ትምህርት ማስጠት ይቻላል፡፡እንደ Rixon (1990) አገላለጽ የተቀረጹ እስፖርታዊ ውድድሮችን ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎች እንዲያዳምጡ ሲደረግ ውጤቱን ለማስማት ይጓጓሉ ፣ ወጥተውም ከጓደኞቻቸው ጋር ማውራት ይፈልጋሉ ፣ቀጥሎ ምን አንደሚመጣ ይገምታሉ ፣ማን ጎል እንዳስቆጠረ ማወቅን ይፈልጋሉ፤ በዚህ ሂደት ውስጥ ንቁ ማዳመጥ ይካሄዳል፡፡ይህም የተማሪዎችን የማድመጥ ክሂል በጥሩ ሁኔታ ያዳብራል፡፡

## 2.7.3 ቀጥተኛ ቃላዊ ገለጻዎች

እንግዶችን ወደ ክፍል በማጋበዝ ወይም ተናጋሪው ወደሚገኝበት አካባቢ በመውሰድ እንዲያዳምጡ የሚደረግበት ሂደት ነው፡ የዚህ አይነቱ ስልት ለተማሪዎች ቀጥተኛውን ቃላዊ ገለጻ ስለሚያቀርብ በርካታ ጥቅሞች ይኖሩታል Underwood {1994) ከእነዚህ ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹ በሚያዳምጡበት ጊዜ ልዩ ልዩ የድምጽ ቅላጼዎችንና የፍጥነት ደረጃዎችን ማስገንዘብ ከሚቀርቡ ንግግሮች ተማሪዎች የንግግር አቅራቢውን ማንንት ፣እድሜ ፣ ስሜት የሚያሳሉትን በማንዘብ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች ምክንያታዊ ምላሽ እንዲሰጡ ያስችላል፡፡

## 2.8.4 ስዕል ካርታ ሰንጠረዥ ሜልክ

ተማሪዎችን ማዳመጥን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፎች ውስጥ በተለያየ ሜልክ ክሂሉን ለማዳበር የሚቀርቡ ይዘቶችም ሌሎች ተጨማሪ ይዘቶችን በምስል ጭምር በማስደገፍ ትምህርቱን ማስጠት ውጤታማ ያደርጋል፡፡እንደ Underwood (1994፣104) አገላለጽ በተለይ ለተማሪዎቹ በይዘትነት የተሚጠት ርዕሰ ጉዳዮች የተማሪዎቹ የእለት ከእለት እንቅስቃሴና ልምድ ጋር የሚይሄዱ ከሆነ በምስል አስደግፎ ማዳመጥን ማስተማር የተሻለ እንደሚሆን አያጠራጥርም ፡፡ ምክንያቱም በይዘትነት የሚቀርበው ምስልም ሆነ ስዕል ተገቢነት ያለው ከሆነ ተማርዎችን በጥንቃቄ እንዲከታተሉና የሚጠየቁትንም ጥያቄ በአግባቡ እንዲሜልሱ በር ይከፈትላቸዋል፡፡እንደ ምሁሩ አገላለጽ እነዚህ ለማስተማሪያነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ምስሎች ወይም መርጃ መሳሪያዎች ካርታ ፣ስዕላ ስእል ፣ሰንጠረዥ፣ የሚያሳሉት ናቸው፡

ከላይ የቀረቡት ምሁር አክለው እንደሚበራሩት ማዳመጥን ለማስተማሪያነት ታስበው ወደክፍል የሚማጡ ስዕሎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በጉልህ የማይታዩ ከሆነ ትምህርቱን ለማስጠት አስቸጋሪ ስለሚሆን ለእያንዳንዱ ተማሪ በሚደርስ ሜልኩ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡በተለይ ማዳመጥን ሳቢነት ባላቸው ምስሎች ስእሎች ማስተማር ፤ማዳመጥን ከጽህፈት ፤ማዳመጥን ከንግግር ለማቀናጀት ጥሩ አጋጣሚ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በተጨማሪም ማዳመጥን ለማስተማር የተመረጡ ይዘቶች ከተማሪዎቹ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴና ልምድ ጋር የሚሄዱ ከሆነ በምስል አስደግፎ ማድመጥን ማስተማር የተሻለ እንደሆነ Underwood (1994) ገልጸዋል፡፡እንደ ምሁሩ አገላለጽ መምህራን ማዳመጥን ሲያስተምሩ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተለያየ ሜልኩ ክሂሉን ለማስተማር የሚያስችሉ ይዘቶች በምስል በማስደገፍ ትምህርቱን ማስጠት ተማሪዎቹ በጥንቃቄ እንዲከታተሉ እና የሚጠየቁትን ጥያቄ በአግባቡ እንዲሜልሱ ያደርጋል ፡፤

## 2.7 በማዳመጥ ትምህርት ጊዜ የመምህራን ተግባር

እንደ Underwood (1989፣21) አገላለጽ ማስተማር ማለት ሁኔታዎችን ማምቻቸት ነው ፡፡ ከዚህም ሌላ የመምህሩ ሚና ለተማሪዎች አስፈላጊውን እርዳታ ማቅረብና ተማሪዎችን መምራት ነው፡ ይህንንም መምህሩ የተለያዩ ተግባሮችን በማዘጋጀት ፣ተማሪዎች በተሻለ መንገድ እንዲያዳምጡ በመርዳትና የትምህርቱን ሂደት ፈተና ባለማስመሳል በራስ የመተማመን ስሜታቸውን በመገንባት ማከናወን ይቻላል፡፡መምህራን በክፍል ውስጥ የማዳመጥ ትምህርትን ሲተገብሩ ትምህርቱን ተጨበጭና አይረሴ ለማድረግ የሚከተሉት ተግባራት ማከናወን አለባቸው (Ur, 2002;35)ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ መምህራን የተደራጁና የታቀዱ አጋጣሚዎችን መፍጠር ይኖርባቸዋል ፡፡ለምሳሌ ተማሪዎች ስለሚያዳምጡት ርዕሰ ጉዳይ ተጨበጭ ምስል እንዲኖራቸው ፡ -

- በተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች በመታገዝ ትምህርቱን ማቅረብ ፡፡
- ስዕላዊ መግለጫዎችን በማጠቀም ማስተማር ፡፡
- በስብሰባ ፣ በውይይት ፤ በጋዜጣ ፣ በካሴት የተቀረጹና የሚደመጡ ይዘቶችን በማቅረብ ማለማመድ ፡፡
- በቅርጻቅርጽ ፣ በፖስተር ፣በካርቶን በማሳሰሉት ማስተማር ፡፡እንደሚገባ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡በተጨማሪም መምህራን ለሚያስተምሩት የትምህርት አላማ የሚመች ይዘት የመምረጥ ፣ የማዘጋጀትና የማሻሻል እድል እንዳላቸው {stern, 1994) ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ እንደ ምሁሩ አገላለጽ መምህር የተዘጋጀለትን የማዳመጥ ትምህርት ማስተማሪያ በማጠቀም ብቻ ትምህርቱን የሚያቀርብ ሳይሆን ይዘቶችን የመምረጥ ሚና ይኖረዋል ፡፡ ከዚህም ሌላ በየክንውኖቹ የሚሰሩ ሜልመጃዎች አመቺ ፣ ተገቢ ፣ ከተማሪዎች ደረጃ ጋር ተመጣጣኝና በተሰጠው ሰአት የሚያልቁ መሆናቸውን መምህራን መገንዘብ እንዳለባቸው (Underwood ፣1989፣25) ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም

Underwood (1989:110) በማዳመጥ ጊዜ የመምህራን ተግባርን አስመልክቶ ሲገልጹ ትረካዎችን ፣ ገለጻዎችን ፣ቃለ ምልልሶችን ፣ ሜና ጨዋታዎች የመሳሰሉትን በማቅረብ ተማሪዎች እንዲለማመዱ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ያስረዳሉ ፡፡ አክለውም ሲገልጹ እውናዊነት ያላቸውን የቋንቋ ግብአቶችን ወደ ክፍል በማምጣት ተከታታይነት ያለውን ልምምድ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ማገዝ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን ተማሪዎች ማድረግና ማወቅ ያለባቸውን ጉዳይ በትክክል ማንዘባቸውን ይቆጣጠራሉ ፡፡ ተማሪዎች አዳምጦ የሚረዳት ጥያቄዎች መመለሳቸውን፣ የቀረቡ ቻርቶች መሙላታቸውን ፣ በራሳቸው አባባልና የአገላለጽ ስልት ተጠቅመው መግለጻቸውን በአግባቡ ይከታተላሉ፡፡

የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር በቅድሚያ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ይጠይቃል ፡፡ ተማሪዎች እንዲያዳምጡ የታሰበውን ንግግር ወይም ምንባብ በአግባቡ ማዘጋጀት ያስፈልጋል ፡፡ስለዚህ ጉዳይ (Rixon 1990 ;66) እና ( Underwood 1889 ;45) የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ዝግጅት ሲደረግ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ማስገባት እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ ፡፡

1 የማዳመጥ ትምህርት አካባቢያዊ ድጋፍ ያለው መሆን ይኖርበታል ፡፡ የማዳመጥ ትምህርት በአካባቢው በሚገኙ የተለያዩ ክንውኖችና ተግባሮች ሙታገዝ ይኖርበታል ፡፡

2 ለማዳመጥ ትምህርት ተብሎ የሚቀርብ ጉዳይ አጩና ማህበብነት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡በክፍል ውስጥ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት በተለይም የማዳመጥ ክሂል ከመምህር መምሪያ ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍና ከሌሎች የጽሁፍ ምንጮች ተወስዶ የሚቀርብ ፣ ይዘቱ ያልተንዛዛ ፣ የሚያስለች ፣ ውበትና ለዛን የተላበሰ መሆን ይገባዋል ፡፡

3 የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚቀርበው ንግግር ወይም ጽሁፍ የተማሪዎችን ፍላጎት ፣አላማና ጠቀሜታን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት ፡፡በክፍል ውስጥ ለማዳመጥ ትምህርት የሚዘጋጁ ጽሁፎች ወይም ይዘቶች ፍላጎትን የሚያነሳሱና የሚቀሰቅሱ እንዲሁም አላማና ጠቀሜታ ያላቸው ቢሆኑ የማዳመጥ ክሂል ትምህርትን ስኬታማ ያደርጉታል ፡፡

4 ለማዳመጥ ትምህርት የሚቀርብ ይዘት ማህተጋብራዊ ግንኙነትን የሚያጠናክርና የሚያበረታታ ሊሆን ይገባል ፡፡

የማዳመጥ ተግባር አጸፋዊና አጸፋ አልባ በማለ በሁለት ይከፈላል ፡፡

- አጸፋዊ የማዳመጥ ተግባር የአድማጩና የተናጋሪዉን ማህተጋብር ወይም ግንኙነት የግድ የሚል ነው ፡፡

- አጸፋ አልባ የሚባለው የማዳመጥ ተግባር ወይም ከአንድ የትምህርት ገለጻ ሬድዮ ፣ ቴሌቭዥን ከመሳሰሉት ሚዲያ የሚገኝበት ነው ፡፡

  ክፍል ውስጥ የሚቀርበው የማዳመጥ ትምህርት በተቻለ መጠን አጸፋዊ የማዳመጥ ተግባር ወይም ክንውን እንዲኖረው አድርጎ ማዘጋጀት አዳምጦ የሚረዳት ክሂልን ያዳብራል፡፡ በአጠቃላይ የማዳመጥ

ክሂልን ለማስተማር የሚቀርበው ዝግጅት የመምህራንን ትጋት ይጠይቃል ፡፡ መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት ፣ እድሜ ፣ እውቀት ወ.ዘ.ተ በማጥናት ተማሪዎቹ የተሻለ የመማር ማስተማር ሁኔታ መፍጠር አለባቸው ፡፡

## 2.8 በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ሚልመጃዎች አቀራረብ

እንደ Rixon (1990) አገላለጽ የማዳመጥ ክሂል ሚልመጃዎች አቀራረብ በቅድመ ማዳመጥ ፣ በማዳመጥ ጊዜ እና በድህረ ማዳመጥ ጊዜ ተብለው በሶስት ይከፈላሉ ፡፡

### 2.8.1 ቅድመ ማዳመጥ

የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ዋና አላማ ተማሪዎች እንዲያዳምጡት ፣ ወደ ተዘጋጀላቸው ጽሁፍ ሐሳባቸውን እንዲሰበስቡና የማዳመጥ ጉጉት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው ፡፡በቅድመ ማዳመጥ ደረጃ ላይ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲያዳምጡት ስለተዘጋጀላቸው ጽሁፍ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ፣በርዕሱ ስር ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ እንደሚችሉ የሚገምቱበት መሆን ይኖርበታል፡፡ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት ለማነሳሳት በጣም አስፈላጊ ናቸው ፡፡ Rixon (1990) እንደሚገልጹት የማዳመጥ ክሂልን በማስተማር ሂደት ውስጥ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ካልተካተቱ የተማሪዎች የማዳመጥ ፍላጎት አይኖርም ፤ ጠቅላላ የማዳመጥ ትምህርት እንዳልተካሄደ መቁጠር ይቻላል ፡፡

በቅድመ ማዳመጥ ወቅት የሚዘጋጁ ሚልመጃዎችን አቀራረብ በተመለከተ Rixon (1990) እና Williams (1984 ) እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ ፡፡

> ከዋናው ርዕስ ጋር የተያያዙ አጫጭር መግቢያ ጽሁፎች ፣ ስለ ርእሱ መገመት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ፣አጠቃላይ ስለጽሁፉ የኋላ ዳራ ለማወቅ የሚያስችሉ ሚልመጃዎች ፤ውይይትን ለማካፈት አመቺነት ያላቸው ጽሁፎች ፣ በአጭሩ በጽሁፍ የሚመልሱ ፣ተማሪዎች የማዳመጥ ፍላጎት እንዲያድርባቸው የሚያስችሉ ፣ የሚያዳምጡበትን ምክንያት እንዲያውቁ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ፣ወደ ማዳመጥ ሂደት ከመግባታቸው በፊት አዳዲስ ቃላትን ለማወቅ የሚያስችሉ እንዲሁም ተማሪዎች የግል አስተያየታቸውን ነጻ ሆነው እንዲሰጡ የሚያስችሉ ሚልመጃዎች ቢካተቱ ሚልካም ነው፡

በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ይዘቱን በማገ እንዲከታተሉና ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡እንደ Underwood (1994) አገላለጽ ቀደምበለው የነበሩት የማዳመት ክሂል ጥያቄዎች ተማሪዎችን በተራክቦ የሚያሳትፉ ሲሆኑ ዝም ብለው እንዲያዳምጡ የሚገፉ ናቸው፡ ይህ ግን በእውነተኛው ህይወታቸው ከሚያጋጥማቸው ተፈትሮአዊ የማዳመጥ ሂደት ጋር የማይጣጣም ነው ፡፡ከዚሁጋር በተያያዘ Yagang(1993፣102) በቅድመ ማዳመት ጊዜ ማሳጠት ያለባቸው የጥያቄ አይነቶች ቀለል ያሉ እና የቅርብ ጊዜ ትውስታን የሚጠይቁ መሆን እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡እንደምሁሩ አገላለጽ በዚህ ጊዜ

የሚቀርቡ ጥያቄዎች ዝግ ጥያቄዎች ፣ቀላል ማከታተያ ቅጽ፣ ስዕሎችን የማየት፣የምርጫ ጥያቄዎች ፣ትክክል /ስህተት ሚለስ የሚሹ ጥያቄዎች ፣የአዎ/አይደለም ጥያቄዎች ቢሆን ይመረጣል፡፡

## 2.8.2 የማዳመጥ ጊዜ

በማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ሚልመጃዎች ተማሪዎች በማዳመጥ ሂደት ውስጥ የሚሚልሷቸው ጥያቄዎች ናቸው፡እንደ Underwood (1994) አገላለጽ በማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ሚልመጃዎች አላማ የተማሪዎችን የአዳምጦ መረዳት ግንዛቤያቸው ከፍ እንዲልና በሚካገሩ ንግግሮች ውስጥ የሚተላለፉ ዋና ዋና ሚልእክቶችን እንዲረዱ የሚያስችሉ ናቸው ፡፡ በማዳመጥ ጊዜ የሚከናወኑ ድርጊቶች በጣም ማራኪና ሳቢ መሆን አለባቸው ፡፡ ተማሪዎች በሚያዳምጡት ነገር ሊመረኩ የሚችሉት ከርዕሱ ጀምሮ በሚቀርብላቸው የታሪክ አወቃቀር ቅደም ተከተል ነው ፡፡ በዚህ ውስጥ አስቂኝ ፣አስደናቂና አስገራሚ ነገሮች የተካተቱባቸው ፣ አብዛኛው ተሚ ሊሚልሳቸው የሚችላቸው ፣ ረዝመው የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚይቀንሱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በማዳመጥ ወቅት ለተማሪዎች ሊቀርቡ የሚገባቸውን ጥያቄዎች በተማላከተ Underwood ( 1994፣50-69) እንዲሁም Rixon (1990 ፣81-90) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፤

- ሰንጠረዦችን በማዘጋጀት ተማሪዎች እያዳማጡ እንዲሞሉ ማድረግ ፤
- በጣም አስፈላጊ መረጃዎችን ብቻ ለይተው እንዲያወጡ ማድረግ ፤
- ተማሪዎችን እያዳማጡ ወደ ተግባር ሊያስገቡ የሚያስችሉ ሚልመጃዎች ፤
- አቅጣጫን ለማወቅ የሚያስችሉ ሚልመጃዎች ፤
- እያዳማጡ ደረጃ ለማስጠት የሚያስችሉ ሚልመጃዎች፤
- የእውነት ሐሰትና የምርጫ ጥያቄዎች ፤
- ጅምር ሐሳቦችን ለማሟላት የሚያስችሉ ሚልመጃዎች፤
- ስህተቶችን እንዲያርሙ የሚያግዙ ሚልመጃዎች፤
- የተናጋሪውን ስሜት ለመረዳት የሚያስችሉ ሚልመጃዎች፤
- ሰዋሰውና ቃላትን ለማስተማር የሚያስችሉ ሚልመጃዎች፡
- የተለያ ጉዳዮችን በየምድቡ መመደብ

## 2.8.3 ድህረ ማዳመጥ

የድህረ ማዳመጥ ሚልመጃዎች የማዳመጥ ሂደት ካበቃ በኋላ የሚቀርቡ ናቸው፡የድህረ ማዳመጥ ሚልመጃዎች አላማ ተማሪዎች የማዳመጥ ጊዜ ክንውኖችን በሚገባ መተግበራቸውንና መረዳት ያለባቸውን ጉዳይ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ፣ ተማሪዎች የተናጋሪውን አማላካከት መረዳት እንዲችሉ ለማድረግ ፣ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር የማሳሰሉት ናቸው፡በድህረ ማዳመጥ የሚቀርቡ ሚልመጃዎች ተማሪዎች ያዳማጡትን ማላስ ብለው እንዲማላከቱ እድል ይሰጣል ፡፡ በቀደምት ጊዜያት ብቸኛ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች የነበሩት የምርጫ

ወይም የክፍት በታ ማሉ ጥያቄዎች እንደነበሩ Underwood (1989) ይገልጻሉ፡፡ አክለውም እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች የሚቀርቡት ማዳመጥን ለማስተማር ሳይሆን ማዳመጥን ለሚፈተን እንደሆነ ያብራራሉ ፡፡በድህረ ማዳመጥ ጊዜ ተማሪዎቹ ለመወያየት ፣ ለማገናዘብና ለመጻፍ በቂ ጊዜ ስለሚኖራቸው በማዳመጥ ጊዜ ከሚቀርብላቸው ጥያቄዎች በተለየ ሚሉ ጠንከር ያሉና ጊዜ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን ማቅረብ እንደሚያስፈልግ Underwood (1989 ) ይገልጻሉ፡፡ በድህረ ማዳመጥ ወቅት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ከቀረበላቸው ምንባብ ማግኘት የሚፈልጉትን መረጃ ማግኘት አለማግኘታቸውን የሚያረጋግጡበት ፣ ውሳኔ ለማጠት የሚስችሉ፣ ተማሪዎች በጥንድ ፣ በቡድንና በጋራ እየተወያዩ፣ እየተከራከሩ በቃል ወይም በጽሁፍ የሚሚሏቸው መሆን እንደሚገባቸው McDonough (1993) ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ ከላይ ምሁራኑ በገለጹት ሀሳብ መሰረት ማዳመጥን ለማስተማር የሚዘጋጁ ከምንባብ የሚወጡ የድህረ ማዳመጥ ሚልመጃዎች የተዘጋጁበትን አላማ ለማሳካት በሚያስችል ሚሉ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል ፡፡ ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ በሚገባ ማዳመጥ አለማዳመጣቸውን ለሚፈተሽ የሚያስችሉ፤ እንዲሁም ተማሪዎች እንዲወያዩ ፣እንዲከራከሩ ፤ሀሳባቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ በማድረግ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር አመቺ የሆኑ መሆን ይኖርባቸዋል ፡፡

## 2.9 የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ምንባቦች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረገባቸው የሚገቡ ነጥቦች

የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚያገለግሉ ምንባቦች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከመካተታቸው በፊት የሚደመጠው ነገር ቋንቋው ፣ ርዝመቱ ፣ ይዘቱ የታሪኩ ፍሰት ሁኔታ ለእውነተኛው አለም መቅረቡ ፣ ወዘተ ማታየት ይኖርበታል በማለት Underwood (1994፣102-105) ያብራራሉ፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች አንድ ጽሁፍ ማዳመጥን ለማስተማሪያነት በመማሪያ መጻሕፍቶች ውስጥ ከመካተቱ በፊት ትኩረት ሊደረገረባቸው የሚገቡ ናቸው ፡፡

### 2.9.1 ቋንቋ

ማዳመጥን ለማስተማር በሚምረጡ ይዘቶች ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ቋንቋ በተመለከተ Underwood (1994 ) እንደሚያብራሩት ማዳመጥን ለማስተማር የምንጠቀምበት ቋንቋ የቋንቋ ለመዳ ሂደትን የተከተለ መሆን ይኖርበታል ፡፡ ምክንያቱም ለተማሪዎች የሚቀርብበት ቋንቋ በሚያውቁት ላይ የተመሰረተ ከሆነ የሚያውቁትን ለሚረዳት ያበረታታቸዋል :: Andersoon እና Lynch (1991 ፣ 9) እንደገለጹት ማዳመጥን ለማስተማር በምንዘጋጅበት ወቅት የምንጠቀምበት ቋንቋ ከተማሪዎች የቋንቋ ችሎታና የትምህርት ደረጃ ጋር በተመጣጠነ ሚሉ መቅረብ አለበት ፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚደመጥ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ለተማሪዎቹ እንግዳ የሆኑና ለሚረዳት የሚያዳግቷቸው አገላለጾች ከተካተቱ ፤የምንባቡን ሀሳብ ሚረዳት ስለሚያዳግታቸው ማዳመጣቸውን ሊያቆሙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ማዳመጥን ለማስተማር የሚዘጋጁ ምንባቦች

የተናጋሪውን ድምጸት ለማየት ፣ለሚረዳት እና የተረዱትን ለመተርጎም እንዲሁም በቀረበው ሀሳብ ማስማማት አለማስማማታቸውን ፣የእነሱ አመለካከት ምን እንደሆነ ለመግለጽ እንዲያስችላቸው ተማሪዎች ሊያዳምጡት የሚችሉትን ቋንቋ ሊይዙ ይገባል፡፡

## 2.9.2 ርዝመት

እንደ Underwood (1994 ፣102) አገላለጽ ለማዳመጥ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ይዘቶች አጠር ቢሉ ይመረጣል ምክንያቱም " ተማሪዎች ያለምንም ማቋረጥ ከተወሰነ ጊዜ በላይ እንዲሰሙ ቢደረግ እያንዳንዱን ነገር ለመከታተል ይቸገራሉ፡፡ "ይህ ማለት ተማሪዎች ለረጅም ጊዜ አያዳምጡም ማለት ሳይሆን የሚቀርበው ነገር የሚረዝም ከሆነ እያንዳንዱን ነገር ለመረዳት የሚደርጉትን ጥረት ያዳክምባቸዋል፡፡በእርግጥ የሚደመጠው ነገር በጣም ሳቢነት ያለው ከሆነ ብዙም ሳይቸገሩ ለረዥም ጊዜ ሊያዳምጡ ይችላሉ ፡፡የሚደመጠው ነገር በጣም አጭር ከሆነም ተማሪዎች የተናጋሪውን ድምጸትም ሆነ ስለምን እንደሚናገር ከራሳቸው ጋር አዋህደው ሳይጨርሱ ያልቃል ይህም ውጤታማ በሆነ መልኩ ማዳመጥን ለማስተማር አስቸጋሪ ያደርገዋል ፡፡ ስለዚህ ማዳመጥን ለማስተማር የሚመረጡ ይዘቶች በጣም ያላጠሩ ወይም ያልረዘሙ መሆን አለባቸው፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ Underwood (1994፣ 103) እንደገለጹት የሚደመጠው ነገር ረጅም ከሆነ ትንሽ ቆም እያሉ ተማሪዎች እየቀረበላቸው ያለውን መረጃ እየተገነዘቡ እንዲሄዱ ማድረግ ይቻላል ፡፡በተመሳሳይ መምህሩ ለተማሪዎች መማሪያነት የተዘጋጀ ምንባብን እያነበበ ማዳመጥን የሚያስተምር ከሆነ እንዴት ባለ ሁኔታ ቆም እያለ በማንበብ መቀጠል እንዳለበት ማዘጋጀት ይኖርበታል ፡፡

## 2.9.3 ይዘት

የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚዘጋጀ የትምህርት ይዘቶች (ምንባቦች) አመራረጥ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ Underwood (1994) ይገልጻሉ ፡፡እንደሳቸው ገለጻ የምንመርጣቸው ይዘቶች የተማሪዎችን የመረዳት አቅም ያላገናዘቡ ከሆኑ ሊተላለፍ የተፈለገው መረጃ ምን እንደሆነ ለመረዳት ይቸገራሉ ፡፡ስለዚህ ማዳመጥን ለማስተማር የሚዘጋጁ ምንባቦች ይዘት የተወሳሰበ ባይሆን ይመረጣል ፤እንዲሁም ቅደም ተከተላቸው ያልጠበቁና የተለያየ ይዘት ያላቸው ጽሁፎችም ካሉ መወገድ ይኖርባቸዋል፡፡

እንደ Underwood (1994) ገለጻ ማዳመጥን ለማስተማር የምንመርጣቸው የትምህርት ይዘቶች አስደሳችና አዝናኝ ቢሆኑ ለመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶች ከዘመኑ ጋር የሚሄዱ አዳዲስ ሐሳቦችን የያዙ ቢሆን ይመረጣል ፡፡ ምክንያቱም አዳዲስ መረጃዎች በሚቀርቡበት ወቅት ሳቢ ስለሚሆን ተማሪዎች የማዳመጥ ፍላጎት ያድርባቸዋል፡፡ በሚቀርብላቸው የሚደመጥ ምንባብ የሚስቡ ከሆነ የማዳመጥ ክሂል ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ክሂሎች ሊዳብሩ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች አዳዲስና ያልተሰለቹ ወቅታዊ መረጃዎች ማዳመጥን ለማስተማሪያነት በሚቀርቡላቸው ጊዜ ተጨማሪ መረጃ

ለማግኘት ያነባሉ ፣ስለርዕሰ ጉዳዩ ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ ወይም በሬድዮ እና በቴሌቭዥን ሲነገር አጋጣሚውን ካገኙ ትኩረት ሰጥተው ያዳምጣሉ ፣ያዳመጡትን በጽሁፍ ወይም በንግግር ለሌሎች መረጃውን ያካፍላሉ፡፡በአጠቃላይ ማዳመጥን ለማስተማር በአግባቡ የተመረጡ ምንባቦች ማዳመጥን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ክሂሎችንም ለማስተማር ያላቸው ሚና የጎላ ይሆናል ፡፡

## 2.9.4 በስዕል የታገዙ ምንባቦች

ተማሪዎችን ማዳመጥን ለማስተማር በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች በስዕል አስደግፎ ማቅረብ ትምህርቱን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡እንደ Underwood( 1994) አገላለጽ ለማስተማሪያነት የተመረጡ ይዘቶች ከተማሪዎቹ የእለት ከእለት እንቅስቃሴ ወይም ልምድ ጋር የሚዩሄድ ከሆነ በስዕል አስደግፎ ማቅረብ አስፈላጊ ነው ፡፡ ተገቢ የሆነ ምስል ከተዘጋጀ ተማሪዎች በጥንቃቄ እንዲከታተሉና የሚከየቁትንም ጥያቄ በአግባቡ እንዲሜሉሱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክትላቸዋል፡፡ እንደ ምሁሩ አገላለጽ በምስልነት ወይም በመርጃ ማሳሪያነት የሚያገለግሉት ካርታ ፣ ስዕላ ስዕል ፣ ሰንጠረዥ የማሳሱት ናቸው፡ እነዚህ መርጃ መሳሪያዎች ተማሪዎቹ ስለቀረበው ርእሰ ጉዳይ ምንም ሚረጃ የሌላቸው ከሆነ በባዶ ከሚያዳምጡ እንዲሁም ሚረጃውን አደራጅተው እንዲያዳምጡ አይናቸውን ይዘ በጆሯቸው የሚባውን ድምጽ ትኩረት እንደሰጡት ያግዛቸዋል ፡፡ እንዲሁም ለሚያዳምጡት ምንባብ ሰንጠረዥ ተዘጋጅቶ እያዳመጡ የተጓደሉ ሚረጃዎችን እንዲሞሉ የሚደረግ ከሆነ ፣ርዕሰ ጉዳዩ ሳቢ ባይሆንላቸው እንኳን ለተጠየቁት ጥያቄ ሚልስ ለማስጠት /ሰንጠረዡን ለማሟላት በሚያደርጉት ጥረት ትኩረት ሰጥቶ የማዳመጥ ክህሎታቸው ከፍ ይላል ፡፡

## 2.9.5 ለትምህርት አሰጣጥ አመቺነት

የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር በመማሪያመጽሐፍ ውስጥ የሚዘጋጁ ምንባቦች ለትምህርት አሰጣጡ አመቺነት ሊኖራቸው ይገባል ፡፡ይህን ሐሳብ Underson and Lynch(1991 ፣19 ) እንደሚገልጹት ውጤታማ በሆነ መንገድ ትምህርትን ማስጠት ያመቻ ዘንድ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ግብአቶች እንደ ሐረጋት ፣ ዓረፍተ ነገሮች ፣ አንቀጾች ያሉት እርስ በእርስ የተዋሀዱ፣ተጠየቂያዊነት ባለው መንገድ የተደራጀ ሐሳብ የያዙ፣ የሚደጋገፉና ተዋረዳቸውን የጠበቁ ሚሆን ይኖርባቸዋል፡፡በመጽሐፍ የሚቀርቡ ታሪኮች ቅደም ተከተላቸውን ያልጠበቁ ከሆነ ታሪኩን አያይዘው አዳምጠው ለመማለስ ይቸገራሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን እንደገለጹት በተለይ በትረካዊ ጽሁፍ ተማሪዎችን ማዳመጥን ማስተማር ከፈለግን የሚረጃዎቹን የተቀናበሩ ሚሆንና ቅደም ተከተላዊነትን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡ የሚቀርበው ጽሁፍ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ያልተደራጀ ከሆነ በተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ የተስተካካለ ምስል የመፍጠር አቅም አይኖርም ፡፡ይህ ካልሆነ ደግሞ የማዳመጥ ፍላጎትን ይቀንሳል ፡፡

## 2.9.6 ለተማሪዎች ቅርበት ያላቸው ይዘቶች

ማዳመጥን በማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የሚያዳምጡትን ነገር በጥሞና እንዲከታተሉ የሚቀርቡ ርዕሶች ለሕይወታቸው የቀረቡ ቢሆን ይመረጣል ፡፡ተማሪዎች ከራሳቸው ህይወት ጋር ቅርብ የሆነና የሚያውቁትን

ነገር በሚያዳምጡበት ወቅት ከራሳቸው ህይወት ወይም ገጠመኝ ጋር በማቀራረብ ስለሚያዳምጡ ትምህርቱን ትኩረት ሰጥተው ሊከታተሉ ይችላሉ፣ እራሳቸውን የድርጊቱ ተሳታፊ በማድረግ ይቆጥራሉ ይህም ጉዳዩ የኔነው ብለው እንዲያስቡ ያስችላቸዋል ፤ ውስጣቸው ላለው ምስል ተጨማሪ ግብአት ለማግኘት ያስችላቸዋል ፣ የህይወት አጋጣሚያቸው ማሻ ስለሚሆናቸው የሚነገረውን መረጃ እንዲሁ ከማስገባት ይልቅ ትክክልና ስህተቱን እየመዘኑ ያዳምጣሉ፡፡ በዚህ ሂደት ስለየሚያዳምጡትን ነገር የተደረጀ ምስል ለመፍጠር ጥረት ያደርጋሉ ፡፡ ተማሪዎች የራሳቸው የህይወት ልምድ ያለበት መረጃ ሲቀርበ የማዳመጥ ክህሎታቸውን ያዳብርላቸዋል፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ አንድ ነገር በከፍተኛ ደረጃ ልሰማው የሚችለውና ውስጡ ሊቀር የሚችለው ከሰው ይልቅ የራሱ ጉዳይ ነው፡ ለምሳሌ ተማሪዎች እንዲያዳምጡት የቀረበላቸው ርእሰ ጉዳይ በማያውቁት ውጪ ሀገር የተከናወነ ከሚሆን ይልቅ በሀገራቸው የተከናወነ ፣ከዚህም ይልቅ ደግሞ በቅብ በሚያውቁት ሰፈር በቅርብ በሚያውቁት ሰው የተከናወነ ሲሆን ፣ ከዚህ በተሻለ ደግሞ እራሳቸው በጉዳዩ የተሳተፍበት ጉዳይ የሚነገር ከሆነ ለሚደማጠው ጉዳይ የሚሰጡት ትኩረት ከአንዱ ወደ አንዱ እየጨመረ ይሄዳል፡፡

ተማሪዎችን ማዳመጥን ለማስተማር የሚቀርቡ ምንባቦች ከክፍል ትምህርቱ ውጪ ባለው ህይወታቸው ሊያጋጥማቸው የሚችል ፣ያዳማጡትን ለመኖር የሚያስችሏቸው ሆነው የሚዘጋጁ ከሆነ የማዳመጥ ክህሎታቸውን ከፍ ለማድረግ ያስችላቸዋል ፡፡

## 2.11 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማጥናት ስትነሳ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ ፣ቋንቋዎች ጥናት ፣ጆርናሊዝምና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን ለመቃኝት ሞክራለች፡፡ ባደረገችው ተመሳሳይነት ያላቸው ርዕሶች አሰሳ የሚከተሉትን ጥናቶች ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን ተቀራራቢነት ያላቸው ስራዎች ሆነው አግኝታቸዋለች፡፡

- ✓ እታገኝ(1986) "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተና እና ግምገማ " በሚል ርዕስ የሁለተኛ ድግሪያቸውን ሰርተዋል ፡፡የዚህ ጥናት ወሰን በ1994 ዓ.ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ያዳብራሉ ተብለው በቀረቡ ይዘቶች ላይ ያተኮረ ነው ፡፡የአጥኚዋ የጥናት ውጤት እንደሚጠቁመው የማዳመጥ ክሂልን ከማስተማር ጋር በተያያዘ በመርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ሜልመጃዎች ችግር እንደሚስተዋልባቸው ነው፡የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ለሚፈጠሩ ችግሮች እንደዋነኛ መንስኤ ሊሆን የችላል በማለት ያነሱት በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ሜልመጃዎች ከአቀራረብ መርሆች አንጻር አሻሚ መሆናቸውን ነው፡ይህም

ሞርሀ ትምህርቱ ለክሂሉ የሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን እንደሚያሳይ ገልጸዋል፡፡ የአታገኝ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል ሞርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ይዘቶችን ትንተና እና ግምገማ ማድረግ ሲሆን ፤ይህ ጥናት ደግሞ ለስምንተኛ ክፍል ለቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ምንባቦችና ማልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው አመቺነት ላይ ነው፤ ስለዚህ ሁለቱ ጥናቶች የማዳመጥ ክሂል ላይ ከማተኮራቸው ውጪ በክፍል ደረጃም ሆነ በትኩረት ነጥቡ ይለያያሉ ፡፡

- ✓ ማስፍን (2000) የዚህ ጥናት አላማ" ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ ማልመጃዎችን ይዘትና አደረጃጀት ሚቲሸ "ሲሆን ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡ጥናቱን ለማከሄድ አይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅመዋል ፤የጥናቱ ውጤት እንደሚያማላክተው ማልመጃዎቹ ከተተግባሪነት ፣ ከቅደም ተከተላዊነት ፣ ከተገቢነት ፣ ወዘተ…አንጻር የተሻሉ ሲሆኑ ከተሰጠው ጊዜ ፣ ከሳቢነትና ከሌሎች ክሂሎች ጋር ከሚያያዝ አንጻር ጉድለት ያለበት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ይህ ጥናት በማዳመጥ ክሂል ላይ ማሰራቱ እና ማልመጃዎች ላይ ትኩረት በማድረጉ ይማሰላል ፤ሆኖም ይህ ጥናት ትኩረቱን በስምንተኛ ክፍል ላይ ማድረጉ እንዲሁም የምንባቦች አቀራረብን ማከተቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡
- ✓ ቶማስ (2002) የጥናቱ አላማ "በኦሮሚያ ክልል በተሚረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለውን የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበር ሁኔታ ሚቲሸ" የሚል ሲሆን ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡ አጥኚው ጥናቱን ለማከሄድ አይነታዊ የምርምር ዘዴን እንዲሁም ተራ የእጣ ንሞና ዘዴን ተጠቅመዋል፡፡ ለሚረጃ ማሰብሰቢያነትም ምልከታን ፣የጽሁፍ ማጠይቅንና ቃለ ማጠይቅን ተጠቅመዋል፡፡ ይህን ጥናት ከቶማስ ጥናት ጋር የሚያማስለው የማዳመጥ ክሂል ላይ በማሰራቱ ሲሆን ለማጥናት በተነሳበት ርዕሰ ጉዳይ፣ በቦታ እንዲሁም በክፍል ደረጃ ልዩነት አላቸው፡
- ✓ አልማዝ (2006)"በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ፣ በሶስት የአዲስ አበባ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ናሞናነት " በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ ጥናት ያቀረቡ ሲሆን ጥናቱን ለማከሄድ በዋነኛነት አይነታዊ ፣ በደጋፊነት ደግሞ ማጠናዊ ምርምሮችን በማጠቀም ፣የእጣ ናሞና አሞራረጥ ዘዴን በማጠቀም ፣ ምልከታንና የጽሁፍ ማጠይቅ የሚረጃ ማሰብሰቢያ ማሳሪያዎችን በማጠቀም ጥናታቸውን አድርገዋል፡፡የአልማዝ ጥናት ትኩረት የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የተዘገጁ ምንባቦችና ማልመጃዎች አቀራረብን ማገምገም ስለሆን እንዲሁም የክፍል ደረጃው የተለያየ በሚሆኑ ሁለቱ ጥናቶች ይለያያሉ፡፡

ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመረጃ ምንጮች አመራረጥ ፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች አይነት ፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ ፣ የአጠናን ስልት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

አጥኚዋ ለማጥናት የመረጠችው ርዕሰ ጉዳይ የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡ ምንባቦችና ከምንባቦቹ የወጡ ጥያቄዎች አቀራረብ ክህሎቱን ለማስተማር ያለውን አመቺነት ስምንተኛ ክፍልን ተተኳሪ በማድረግ መፈተሽ ነው ፡፡

ጥናቱ የያዘውን አላማ ከግብ ለማድረስ ተግባራዊ የተደረገው የአጠናን ዘዴ ቅይጥ የምርምር ዘዴ ሲሆን በዋናነት ከአይነታዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ አንዱ የሆነውን ገላጭ የምርምር ስልት( Descriptive Research ) በደጋፊነት መጠናዊ ምርምር በጥቅም ላይ ውሏል ፡፡ በዚህ ጥናት ቅይጥ ምርምር ዘዴ ያስፈለገበት ምክንያት ምርምሩ የሚተነተነው በገለጻና በቁጥር መረጃ ስለሆነ ነው ፡፡ በመሆኑም አይነታዊ ምርምር ዘዴን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት የጥናቱ አቀራረብ ገላጭ ስልትን የተከተለ በመሆኑ ነው፡አጥኚዋ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር በመማሀሩ መማሪያ የቀረቡ ምንባቦችን ፣ ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎች እንዲሁም የክፍል ምልከታ በማድረግ አቀራረቡ ላይ ጥናት በሚደረግበት ወቅት ለግምገማው በሚዘጋጁት መስፈርቶች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎችን በገለጻ ስልት መተንተን አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ ነው ፡፡ መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኚዋ በቁጥር ለምትገልጸው የመረጃ ትንተና አመቺ ሆኖ ስላገኘችው ልትመርጠው ችላለች፡፡

## 3.2 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት ፣ በመማሀራን የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ ፣ ከምልከታ የማገኙ የመረጃ ግብዓቶች ናቸው ፡፡ እንዲሁም በንድፈ ሀሳባዊ ማሰረቶች እና የድህረ ምረቃ ጥናቶች ፣ድህረገጽ እና የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር የጥናት መጻሕፍት ምርምር ላይ በመመስረት ነው ፡፡በመሆኑም የሚፈለጉት መረጃዎች ለጥናት ለተመረጠው የክፍል ደረጃ ከቀረበው መጽሀፍ ፣ ከክፍል ምልከታ ፣ ከጽሁፍ መጠይቅ ፣ከድህረ ምረቃ ጥናቶች ፣ከተለያዩ

መጻሕፍት ፣ከድህረ ገጾች ከተሰበሰቡ በኋላ በአስፈላጊው ቅደም ተከተል ተዘርዝረው በገላጭ ስልት ትንተና ተሰጥቶባቸዋል ፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

### 3.3.1 የጥናቱ ክልል አመራረጥ

አጥኚዋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ለብዙ አመታት በመምህርነት ሙያ የሰራች በመሆኑ ከመምህራን አገኛቸዋለሁ ብላ ያሰበቻቸውን መረጃዎች ከሌሎች ክፍለ ከተማዎች በተሻለ ሙሉ መረጃዎችን ማግኘት እንደምትችል በማመኑ የአቃቂ ቃሊቲን ክፍለ ከተማን የጥናቱ ክልል እንዲሆን በአመቺ የንሞና ዘዴ መርጣ የጥናቱ ቦታ እንዲሆን አድርጋለች፡፡

### 3.3.2 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኙ አራት የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶችን ለዚህ ጥናት በሚረዳ ምንጭነት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት አመቺ የናሙና ስልትን ማዕረት በማድረግ ነው፡ ሶስቱ ትምህርት ቤቶች አጥኚዋ የሰራችባቸው መሆናቸው እና አንዱ ትምህርት ቤት ደግሞ ለመኖሪያ አካባቢዋም ቅርበት ያለው በመሆኑ መረጃዎችን ለማሰብሰብ አመቺ ይሆናል ብላ በማመኑ ነው ፡፡ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች አቃቂ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣ አዬ ቴዎድሮስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣ አለም ብርሀን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ብሩህ ተስፋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡

### 3.3.3 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

አጥኚዋ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመምህርነት ስታገለግል ቆይታለች ፡፡ በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በአገልግሎት ላይ ያለውን የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍ በቅርበት ታውቀዋለች፡፡ ስለሆነም የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ማዳመጥን በምታስተምርበት ጊዜ ክህሎቱን ለማስተማር የተዘጋጁትን ምንባቦችን ለማዳመጥም ሆነ ከምንባብ የወጡ ሙሉመጃዎችን ለማስራት ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ መሆኑን ማስተዋል ችላለች ፡፡ ስለዚህ ችግሩ የተፈጠረበትን ምክንያት ሳይንሳዊ መርሆችን በመከተል መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ በመሆኑም የስምንተኛ ክፍል መማሪያ እና ማስተማሪያ መጽሐፍ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጧል፡፡

### 3.3.4 የመምህራን አመራረጥ

በ2017 ዓ.ም በአቃቂ መንግስት ፣ በአዬ ቴዎድሮስ ፣ በአለም ብርሀን እና በብሩህ ተስፋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጠቅላይ የናሙና ስልት በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል ፡፡

## 3.4 መረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎች

አጥኚዋ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ እና ተገቢ ናቸው ብላ ያመነችባቸው ሶስት የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎች በስራ ላይ ውለዋል ፡፡እነሱም የሰነድ ፍተሻ ፣ የጽሁፍ መጠይቅ እና ምልከታ ናቸው ፡፡ ከእነዚህ የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎች መካከል የሰነድ ፍተሻ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቅና ምልከታ ደግሞ በአጋዥነት አገልግለዋል ፡፡

### 3.4.1 የሰነድ ፍተሻ

የሰነድ ፍተሻ ለዚህ ጥናት አላማ ከግብ መድረስ ዋናውን ድርሻ የያዘ ነው፡ይህም የሚያተኩረው በስምንተኛ ክፍል ማስተማሪያና መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ምንባቦችና ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎች አቀራረብን በተለያዩ መረጃዎች አስደግፎ በመተንተን ላይ ይሆናል ፡፡ለዚህም እንዲያግዝ የማዳመጥ ክሂል ምንባቦች እና መልመጃዎች አቀራረብ በተለያዩ ንድፈ ሐሳቦች አማካኝነት ተቃኝተዋል ፡፡ከዚህም በተጨማሪ ንድፈ ሀሳቦቹን መሰረት ያደረጉ የመገምገሚያ መስፈርቶች ተዘጋጅተዉ ጥቅም ላይ ውለዋል ፡፡ ይኸውም የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ምንባቦች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦች ፣ የመልመጃዎች አቀራረብና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው እገዛ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ፡፡

### 3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ

ለመምህራን የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የተነሱትን ጽንሰ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡ መጠይቁ ከሰነድ ፍተሻው የተገኘውን መረጃ ለማጠናከርና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ታስቦ ተግባራዊ የሆነ ነው ፡፡ በመሆኑም ለዚህ አላማ የሚውሉ የጽሁፍ መጠይቆች በዝግ ወይም ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎችንና በልቅ ወይም በነጻ የአቀራረብ ስልት ተዘጋጅተው ለጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ቀርበው ምላሽ እንዲሰጥባቸው ተደርጓል ፡፡እነዚህን የአጠያየቅ ስልቶች መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ዝግ የአጠያየቅ ስልት በቀላሉ ለመተንተን አመቺ በመሆኑ ሲሆን ልቅ የአጠያየቅ ስልትን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ መላሾቹ ሐሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ስለሚያስችል በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃዎች ለማግኘት ስለሚረዳ ነው ፡፡ የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ከተደረጉ አስራ አንድ መምህራን መካከል ሁለቱ ውጠቁን ያልመለሱ በመሆናቸው ሁለቱን ከጥናት ውጪ እንዲሆኑ በማድረግ በዘጠኙ መምህራን የተገኘው መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 3.4.3 ምልከታ

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ከመማር ማስተማሩ ሂደት ለማሰባሰብ ምልከታ በዋናነት የሚመረጥ ዘዴ ነው፡የምልከታው አላማም የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥ ክሂልን በሚያስተምሩበት ወቅት ሆን ብለውና አቅደውበት በቅድመ ማዳመጥ ፣ በማዳመጥ እና በድህረ ማዳመጥ ወቅት ተገቢውን የአቀራረብ ስልት መከተል አለመከተላቸውን ለመረዳት ነው ፡፡

ምልከታው የተደረገው በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሲሆን ሁሉም የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተካተዋል፡፤ ለምልከታው የሚያገለግለው ቅጽም የተዘጋጀው ከ Underwood (1989) ሐሳብ በመውሰድ የማዳመጥ ክሂልን የክፍል ውስጥ አቀራረብ ስልቶች ማሰረት ያደረገ ነው ፡፤ የማካታተያ ቅጹን በማጠቀም በናሙናነት በተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ ስድስት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሶስት ሶስት ጊዜ ያህል በድምሩ ለስራ ስምንት ጊዜ ምልከታው ተካሂዷል፡፡ከተመረጡት አስራ አንድ መምህራን ማካከል በስድስቱ ላይ ብቻ ምልከታው የተካሄደበት ምክንያት አምስቱ መምህራን ፍቃደኛ ሆነው ባለማኘታቸው ነው፡ በምልከታው የተገኘውን መረጃ አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ከአጥኚዋ በተጨማሪ የመጀመሪያ ድግሪ ያለቸው ሁለት የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምልከታው በሚደረግበት ክፍል ውስጥ በማኘት እገዛ አድርገዋል፡፡ከአጋዥ መምህራኑ ጋርም ምልከታው ከማካናወኑ በፊት ውይይት ተደርጎ ስለ አሰራሩ መረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህ ማሰረት መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በአስራ ስምንቱ ምልከታ ጊዜያት ለማካታተያ የተዘጋጁት ነጥቦች በሶስት ክፍለ ጊዜያት በጣም ከፍተኛ ፣ ከፍተኛ ፣ ማካከለኛና ዝቅተኛ ውጤቶች እንደተማዘገቡ በመቁጠርና በመቶኛ በማአወጥ ውጤቶቹ ተደምረው ለትንተና ቀርቧል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን መረጃዎች ለመተንተን ገላጭ የመተንተኛ ስልት በጥቅም ላይ ውሏል ፡፡ በመሆኑም በማዛግብት ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ንድፈ ሀሳቦችና ከአጥኚዋ እይታ አንጻር በገላጭ የአተናተን ስልት ከተተነተኑ በኋላ የጽሁፍ ማጠይቁን ከሞሉት መምህራን እይታ አንጻር የተገኙት መረጃዎች የቁጥር ማአኪያ ተሰጥቷቸው በመቶኛ ተገልጸዋል ፡፡እንዲሁም በጽሁፍ ማጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደአስፈላጊነቱ በትንታኔው ጣልቃ መግባት በሚገባቸው ቦታ እየተተነተኑ ቀርበዋል፡፡ የክፍል ምልከታው በአራት ክፍሎች ውስጥ አቀራረብን በተማአከተ ከመምህራን የጽሁፍ ማጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በገላጭ የአተናተን ስልት የቀረቡ ሲሆን በክፍል ውስጥ የተገኙ መረጃዎች ከአጥኚዋ እይታ አንጻር የቁጥር ማአኪያ ተሰጥቷቸው በመቶኛ ከተተነተኑ በኋላ በገላጭ የአተናተን ስልት ቀርበዋል ፡፡ የትንተናው ትኩረት የማዳመጥ ክሂል ምንባቦችና ከምንባብ የወጡ መልመጃዎች አቀራረብ ላይ ነው ፡፡ ይኸውም ትኩረት ያደረገው የምንባቦቹ ይዘት ለተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ተስማሚ ናቸው ? አቀራረባቸው ሳቢነት አለው ? የተለያዩ የማስተማሪያ ማሳሪያዎች ተካተውበታል ? የመልመጃዎቹ አቀራረብ ክሂሉን ለማስተማር ያለው እገዛ እንዴት ነው? የሚሉት ነገሮች በዋነኛነት ትኩረት ተደርጎባቸዋል ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

### 4.1 መግቢያ

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተገለጸው የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ በዋናነት የሰነድ ፍተሻ ሲሆን አጋዥ የመረጃ ማሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ደግሞ የጽሁፍ ማጠይቅና ምልከታ ናቸው፡ አጥኚዋ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍን እና የመምህሩን መምሪያ  የሰነድ ፍተሻ በማድረግ ፣የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደትን በመመልከትና ለመምህራን የጽሁፍ ማጠይቅ በመቅረብ መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡የዚህ ክፍል አላማም የተሰበሰቡትን መረጃዎች መተንተን ነው፡፡

### 4.2 አዳምጦ መረዳት ምንባቦች ግምገማ

ለአንድ የክፍል ደረጃ የሚቀርቡ አዳምጦ የመረዳት ምንባቦች ሲዘጋጁ ተማሪዎች የሚያውቁትና በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ የቀረበ ፣ በጣም አጥረው ስለምን እንደሚገለጽ ከራሳቸው ጋር አዋህደው ከሚጨርሳቸው በፊት እንዳያልቅ ፤ ወይም በጣም ረዝመው አሰልቺ እንዳይሆኑ ርዝመታቸው የተመጠነ ፣ ያልተወሳሰቡ እና ለመረዳት የማያስቸግሩ ይዘቶችን ፣ ሐረጋትና አረፍተ ነገሮች እርስ በእራሳቸው የተዋሐዱ ፣ ታሪኩ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ለትምህርት አሰጣጡ አመቺ የሆነ ፣ ምንባቦቹ የያዙት መረጃ ከተማሪዎች ህይወትና ገጠሚኝ  ጋር ቅርበት ያለውና የኔ ነው በማለት የሚከታተሉት እንዲሁም በምስሎችና ስእሎች የታገዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ አለበለዚያ ክህሎቱን የማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

በ2015ዓ/ም በተግባር ላይ የዋለው የስምንተኛ ክፍል ማስተማሪያ መጽሐፍ በአስር ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በውስጡ አስር የአዳምጦ መረዳት ምንባቦችን ይዟል፡፡ ማስተማሪያ መጽሐፉ ከምንባቦቹ በተጨማሪ የማስተማሪያ መመሪያዎችን እንዲሁም የማዳመጥ ጊዜ ጥቄዎችን ይዟል፡፡ በሚሆኑም የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር በማስተማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት ምንባቦች አቀራረብ ክሂሉን ለማስተማር አመቺ ናቸውን? ለሚለው ጥያቄ ምላስ ይሆን ዘንድ ከመረጃ ምንጮች የተገኘው መረጃ  እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 4.2.1 አዳዲስ መረጃዎችን ስለሚያዘቸውና በስፋት የመቅረብ ሁኔታ

አዳምጦ የመረዳት ክሂልን ለማስተማር ለተማሪዎች የሚዘጋጁ ጽሁፎች የትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጽሁፎቹ (ምንባቦቹ) ሲመረጡ የተማሪውን ጆሮ የመሳብ አቅም ሊኖራቸው ይገባል ፡፡ ይህም እንዲሆን ርዕሰ ጉዳዮቹ አዲስና ያልተሰለቹ ቢሆን ምልካም

ነው ፡፡ በስምንተኛ ክፍል የማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አስር ለማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያነት የቀረቡ ምንባቦች አሉ፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡

- ✓ ሰው ለስራ
- ✓ ቅርሶች በኢትዮጵያ
- ✓ ዶክተር ካትሪን ሐምሊን
- ✓ የሕይወት ቅዳጆች
- ✓ የህዝብ ቁጥር ሚጨምር እንደሚልካም አጋጣሚ
- ✓ የምድራችን ጀግና
- ✓ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ እና ህገወጥ ዝውውር
- ✓ ሰላምን ፍለጋ
- ✓ የአየር ንብረትና የአካባቢ ብክለት
- ✓ ለሁሉም ጊዜ አለው (ተውኔት)

እነዚህ ለአስሩም ምዕራፎች አንድ አንድ የተጋጁት የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የቀረቡ ጽሁፎች ለአንብቦ ሚረዳት ከቀረቡት ምንባቦች ጋር የሀሳብ ተማሳሳይነት አለቸው ፡፡ ለምሳሌ ምዕራፍ 1 <<የስራ ሥነ ምግባር >> አጠቃላይ ርእስ ስር <<የአውራምባ ማህበረሰብና ማለጮው >> የሚል የአንብቦ ሚረዳት ምንባብ ቀርቧል በዚሁ ምዕራፍ ስር <<ሰው ለስራ >>የሚል የማዳመጥ ክሒልን ለማዳበር የተዘጋጀ ምንባብ ቀርቧል፡፡ምዕራፍ 5 <<ሥነ ሕዝብ>> በሚል የቀረበ አጠቃላይ ርዕስ ስር <<የኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ>> የሚል የአንብቦ ሚረዳት ምንባብ ቀርቧል ፡፡ በዚሁ ምዕራፍ ስር <<የህዝብ ቁጥር ሚጨምር እንደ ሚልካም አጋጣሚ>> የሚል የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጀ ምንባብ ቀርቧል፡፡ ምዕራፍ 6 <<በረሀማነት >>በሚል የቀረበ አጠቃላይ ርዕስ ስር <<ተፈጥሮን የመማስ ስራ >> የሚል ርዕስ ያለው ምንባብ ለአንብቦ ሚረዳት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረበ ሲሆን ፤ በመምህሩ መምሪያ ደግሞ <<የምድራችን ጀግና>> በሚል ርዕስ ለአዳምጦ ሚረዳት የቀረበ ጽሁፍ አለ ፡፡ጽሁፉ በብዝኃ ህይወት አጠባበቅ ላይ በጥልቀት የሰሩ ግለስብ የሚተርክ ነው፡ ምዕራፍ 7 <<የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ >> አጠቃላይ ርዕሱ ነው፡ በስሩም የአንብቦ ሚረዳት ምንባብ ቀርቧል፡- <<የሚርቱ እና የማሳሎቿ ፍዳ >> በሚል ርዕስ ፡፡ ለአዳምጦ ሚረዳት የቀረበው ምንባብ ደግሞ <<የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውር በከተማችን>> የሚል ነው፡ ምዕራፍ 9 <<የአየር ንብረት>> አጠቃላይ ርዕስ ስር <<የአየር ንብረት ለውጥና ችግሮቹ >> ፣ ለአንብቦ ሚረዳት የቀረበ ምንባብ የቀረበ ሲሆን በመምህሩ መምሪያ ደግሞ << የአየር ንብረትና የአካባቢ ብክለት >> የሚለው ደግሞ ለአዳምጦ ሚረዳት የቀረበ ምንባብ ነው፡ ሌሎቹም በተማሳሳይ ለአንብቦ ሚረዳት ከቀረቡት ምንባቦች ጋር የሀሳብ አንድነት አላቸው፡ እዚህ ሚረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ ማዳመጥን በሚማሩበት ጊዜ የተለየ ርዕሰ ጉዳይ

አያገኙም፡ ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች ይዘታቸው ተማሪዎቹ በተደጋጋሚ በማሪያ መጽሐፋቸው ለአንብቦ ሚረዳት ቀርበውላቸው ያነበቧቸው ስለሆኑ የማዳመጥ ጉጉትን አይቀሰቅሱም፡ የማዳመጥ ክሂል ምንባቦች በስፋት የሚቀረባቸው ሁኔታን በተማለከተ፣ በየምዕራፉ አንድ አንድ የቀረበ ስለሆነ በአጥኚዋ ግምት ማነረት በቂ ናቸው፡ይህን በተማለከተ ከማምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 2 ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁ ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ተማጣጣኝ ስለሚሆናቸው፣ሳቢነትና በስፋት ሙቅረብ በተማለከተ

| | ማጠይቆች | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
|---|---|---|---|
| 1 | በማምህሩ ማምሪያ የቀረቡት ምንባቦች የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ናቸው | | |
| | 1 በጣምእስማማለሁ | - | - |
| | 2 እስማማለሁ | 2 | 22.2 |
| | 3 አልስማማም | 6 | 67 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | 1 | 11.1 |
| | ድምር | 9 | 100 |
| 2 | የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች በቂ በሆነ ሁኔታ ቀርበዋል | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | 1 | 44.4 |
| | 2 እስማማለሁ | 4 | 44.4 |
| | 3 አልስማማም | 3 | 22.2 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | 1 | 11.1 |
| | ድምር | 9 | 100 |
| 3 | በማምህሩ ማምሪያ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ምንባቦች አዳዲስ ሚጃዎችን ይዘዋል | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | - | - |
| | 2 እስማማለሁ | 3 | 33.3 |
| | 3 አልስማማም | 4 | 44.4 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | 2 | 22.2 |
| | ድምር | 9 | 100 |

ከሰንጠረዥ 2 ከተገኘው መረጃ እንደምንረዳው ማዳመጥን ለማስተማር በመማህሩ መምሪያ የቀረቡት ምንባቦች የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ስለመሆናቸው ለቀረበው ጥያቄ 67% የሚሆኑት በቀረበው ሐሳብ እንደማይስማሙ እና 11.1 % የሚሆኑት ፍጹም እንደማይስማሙ የገለጹ ሲሆን 22.2% የሚሆኑት ደግሞ በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልጸዋል ፡፡ አብዛኛው መምህር ከሰጠው ምላሽ አንጻር ለማስተማሪያነት የቀረቡት ምንባቦች የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ አይደሉም ፤ ስለዚህ ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡

ማዳመጥን ለማስተማሪያነት የቀረቡት ምንባቦች በቂ ስለመሆናቸው ለቀረበው ጥያቄ 44.4% የሚሆኑት በጣም እንደሚስማሙ 44.4 % ደግሞ በቂ ናቸው በሚለው ሀሳብ የሚስማሙ መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን 22.2% የሚሆኑት እንደማይስማሙ ፣11.1% የሚሆኑት ደግሞ በቂ ምንባቦች ለማስተማሪያነት ቀርበዋል በሚለው ሀሳብ ፈጽሞ እንደማይስማሙ ገልጸዋል ፡፡ ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በምንባቦቹ በቂ መሆን ላይ መምህራኑ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊም አሉታዊም ነው፡

በመማህሩ መምሪያ ላይ የቀረቡት ምንባቦች ለተማሪዎቹ አዲስ የሆኑ መረጃዎችን ስለመያዛቸው ለመማህራን ለቀረበው ጥያቄ 44.4% የሚሆኑት እንደማይስማሙ ፣22.2% ፍጹም እንደማይስማሙ የገለጹ ሲሆን 33.3% የሚሆኑት ደግሞ በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልጸዋል፡፡ የሰነድ ፍተሻው እንደሚያስረዳው ከመማህራኑ የተገኘው ምላሽም እንደሚያረጋግጠው ማዳመጥን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች ተማሪዎቹ የሚያውቋቸውን አዳዲስ መረጃዎች የያዙ አይደሉም ፡፡ ምክንያቱም ለማዳመጥ ማስተማሪያነት የቀረቡት ምንባቦች ለአንብቦ መረዳት ማስተማሪያነት በመማሪያ መጽሐፋቸው ከቀረቡት ምንባቦች ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ አላቸው ፡፡ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው መረጃዎች መብዛታቸው የማዳመጥ ፍላጎትን ከማነሳሳት ይልቅ አዲስ ነገር የለውም በሚል ስሜት ማዛናጋት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡

### 4.2.2 ስነ-ጽሁፋዊ ይዘቶችን የማከተታቸው ሁኔታ

ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ማዳመጥን ለማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፤ ምክንያቱም ስነ-ጽሁፍ ካለው እያዝናና መረጃን የማቀበል ባህሪው የተነሳ የተማሪዎችን ቀልብ የመሳብ ኃይል አለው፡ በዚህ የተነሳ መማህሩ ጽሁፉን ሲያነብ ተማሪው ትኩረት ሰጥቶ ያዳምጣል፡፡ ይህም ተማሪዎች የሚነገረውን መረጃ በአግባቡ እንዲከታተሉና የማዳመጥ ችሎታውን እንዲያዳብሩ በር ይከፍትለታል (በድሉ፤1996፣6) ይህን መነረት በማድረግ ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር በመማህሩ መምሪያ ከቀረቡት አስር ጽሁፎች ውስጥ አራቱ ስነጽሁፋዊ ይዘት ያላቸው ናቸው ፡፡ ሆኖም የያዙት መረጃ ፍዝ ነው፡ ለምሳሌ፡- በምእራፍ 4 <<አጫጭር ልቦለድ>> በሚለው አጠቃላይ ርዕስ ስር<<የህይወት ቅዳጆች>>የሚል ለአዳምጦ መረዳት የቀረበ ፅሁፍ አለ፡፡ፅሁፉም በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የተሜሩትን የአጫጭር ልቦለድ ልዩ በሀሪ የሆነውን ነጠላ ውጤት የለውም ከዚህ በተጨማሪ ወቅታዊነት ይጎድለዋል፡፡ በ2015 ዓ.ም. የታተመ መፅሐፍ በዘመኑ የማይገኝ የቤት ኪራይ ዋጋ በወር 120ብር፣በወር30ብር የአልጋ ኪራይ እና የ1ብር ስኳር የሚሉ ገለፃዎች ለአዳምጦ መረዳት በቀረበ ፅሁፍ ውስጥ ተካተዋል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን

የማዳመጥ ፍላጎትን ይቀንሰዋል ፡፡ በመምህሩ መምሪያ ከቀረቡት እና ስነጽሁፋዊ ይዘት ካላቸው የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ ምንባቦች ውስጥ በአጥኚዋ አማካከት የተሻለ የማዳመጥ ፍላጎትን የሚያዝ አቅም ያላቸው << ለሁሉም ጊዜ አለው! >> ተውኔት እና <<ዶክተር ካትሪን ሐምሊን>> ታሪክ ናቸው ፡፡ ይህን አስመልክቶ ለመምህራን ከቀረበው የጽሁፍ ማጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 3 የማዳመጥ ክህሎትን ለማዳበር በመምህሩ መምሪያ የቀረቡት ጽሁፎች ስነጽሁፋዊ አቀራረብ ስለሚያዛቸው

| | ማጠይቅ | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
|---|---|---|---|
| 1 | ስነጽሁፋዊ አቀራረብን ተላብሰው ለማስተማሪያነት የቀረቡት ማዳመጥን ለማስተማር የቀረቡ ጽሁፎች ክፍሎቱን ለማስተማር አመቺ ናቸው | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | 3 | 33.3 |
| | 2 እስማማለሁ | 4 | 44.4 |
| | 3 አልስማማም | 2 | 22.2 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | - | - |
| | ድምር | 9 | 100 |

ማዳመጥን ለማስተማር የቀረቡት ጸሁፎች ስነ-ጽሁፋዊ ይዘትን ተላብሰው በመቅረባቸው ማዳመጥን ለማስተማር ያላቸውን ፋይዳ በተመለከተ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቧል ፡፡ የሰጡትንም ምላሽ ከሰንጠረዥ 3 መረዳት እንደሚቻለው 33.3% የሚሆኑት መምህራን በጣም እንደሚስማሙ ፣44.4% የሚሆኑት እንደሚስማሙ የገለጹ ሲሆን 22.2% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የአብዛኛዎቹ መምህራን ምላሽ እንደሚያመለክተው ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች ስነጽሁፋዊ አቀራረብ መያዛቸው ማዳመጥን ለማስተማር አመቺ እንደሆነ ነው፡ከመምህራኑ የተገኘው ምላሽ አጥኚዋ ከሰነድ ፍተሻው በማሳት ካላት አማካከት ጋር ልዩነት አለው፡

## 4. ቋንቋ እና ይዘት

ማዳመጥን ለማስተማር የሚቀርቡ ጽሁፎች ማዘጋጀት ያለባቸው ተማሪዎች መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እና የትምህርት ደረጃቸውን ያገናዘበ በሆነ መልኩ ነው ፤ በተጨማሪም የትምህርት ይዘቶቹ ከዘሙ ጋር የሚሄዱ አዳዲስ ሐሳቦችን የያዙ፣ ያልተወሳሰቡና የተለያየ ሀሳብ ያልያዙ ፣ ለመረዳት የማያስቸግሩ ሳቢነት ያላቸውና ከተማሪዎች እድሜ ጋር የሚሄዱ መሆን እንዳለባቸው በምዕራፍ ሁለት ተጠቅሷል፡፡ ምክንያቱም ምንም አይነት ጠቃሚ መረጃዎችን የያዙ ጽሁፎች ቢሆኑ ተማሪው ሊሸከሙ ከሚችለው የእውቀት

ደረጃ በላይ ከሆኑ ክህሎቱን ለማዳበር ያላቸው ጠቀሜታ አጠራጣሪ ይሆናል፡፡ በክፍሉ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች እኔን ይመለከታል ወይም የኔ ጉዳይ ነው ብለው የሚያዳምጡት የምንባብ ይዘት ለትምህርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፡፡ በሰነድ ፍተሻ ለሚረዳት እንደተቻለው ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር በመማሀሩ ማምሪያ ከቀረቡት ምንባቦች በአብዛኛው ከተማሪዎች የእድሜ የትምህርት ደረጃ ጋር ተመጣጣኝና ለሚረዳት አዳጋች ያልሆኑ ናቸው፡ ሆኖም አንዳንድ ምንባቦች መሻሻል የሚገባቸው ናቸው ለምሳሌ <<የሕይወት ቅዳጆች>>የሚለው ጽሁፍ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መረጃ ለሚረዳት ያስቸግራል ፤ ምክንያቱም ለጽሁፉ አጋዥ ሆኖ የቀረበው ስዕል አንድ ሠው ባዶ ቤት አልጋ ላይ ተዘርግቶ ሞቶ ይሆን በሕይወት ያለ በግለፅ አያሳይም፡ወደ ምንባቡ ሲገባም ሠለሞን የሚባል የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ወደ ቤቱ እንደ ገባ አልጋ ላይ ተንጋለለ ፡፡ቀጥሎም እንደ ደከመው እና በርካታ ሐሳብ በውስጡ እንደሚመላለስና ዓይኑን ቢጨፍን እንኳን መተኛት እንዳልቻለ ፅሁፉ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ከርዕሱ እና ከቀረበው ስዕልና ማብራሪያ አንፃር ሠለሞን የገጠመውን ነገር ምን እንደሆነ አያሳየም፡ለተማሪዎች ምንም የሚያስተላልፈው መልእክት የለውም፡ በመሆኑም አዳምጠው ሲጨርሱ ለጥያቄዎች መልስ አይሰጡም ፡፡ ስለዚህ ይህ ጽሁፍ ከይዘት አንጻር ደካማ ነው ፡፡ ትምህርትን የማያበረታታ ጽሁፍ ለተማሪዎች በማቅረብ ማስተማር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር በመማህሩ መምሪያ የቀረቡ ጽሁፎች የቋንቋ እና የይዘት ሁኔታ የተማሪዎችን የሚረዳት አቅም ያገናዘበ ስለመሆኑ ለመምህራን ከቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 4 የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር የቀረቡት ጽሁፎች ቋንቋ እና ይዘት የተማሪዎችን የሚረዳት አቅም ያገናዘበ ስለመሆኑ

| | ማጠይቆች | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
|---|---|---|---|
| 1 | ክህሎቱን ለማስተማር የቀረቡ ምንባቦችና ከምንባብ የወጡ መልመጃዎች የቀረቡበት ቋንቋ ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት ነው | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | 2 | 22.2 |
| | 2 እስማማለሁ | 4 | 44.4 |
| | 3 አልስማማም | 3 | 33.3 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | - | - |
| | ድምር | 9 | 100 |
| 2 | የማዳመጥ ክሂል ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ የትምህርት | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | እና የእድሜ ደረጃ ጋር ይስማማሉ | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | - | - |
| | 2 እስማማለሁ | 2 | 22.2 |
| | 3 አልስማማም | 4 | 44.4 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | 3 | 33.3 |
| | ድምር | 9 | 100 |

ከሰንጠረዥ 4 የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦችና ከምንባቦቹ የወጡት ጥያቄዎች የቀረቡበት ቋንቋ ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት ስለመሆኑ ለመምህራን ከቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ 44.4% የሚሆኑት እንደሚስማሙ እና 22.2% የሚሆኑት ደግሞ በጣም እንደሚስማሙ የገለጹ ሲሆን 33.3% የሚሆኑት መምህራን ደግሞ ምንባቦቹ እና ጥያቄዎቹ የቀረቡበት ቋንቋ በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችል ነው በሚለው ሀሳብ እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ ከአብዛኛዎቹ ምላሾች መረዳት እንደሚቻለው ምንባቦቹ እና ከምንባቦቹ የወጡት ጥያቄዎች የቀረቡበት ቋንቋ ለመረዳት የማያዳግታቸው መሆኑን ነው፡

የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች ከተማሪዎቹ የትምህርት እና የእድሜ ደረጃ ጋር መስማማታቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 22.2% የሚሆኑት እንደሚስማሙ የገለጹ ሲሆን 44.4% የሆኑት እንደማይስማሙ ፤33.3 % የሚሆኑት መምህራን ደግሞ ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ የእድሜና የክፍል ደረጃ ጋር ይሄዳሉ በሚለው ሀሳብ ፈጽሞ እንደማይስማሙ ገልጸዋል ፡፡ አብዛኛዎቹ መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ክሂሉን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች ከተማሪዎቹ እድሜና የክፍል ደረጃ ጋር የመጣጣም አቅማቸው አነስተኛ መሆኑን ነው፡ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃም የሚያረጋግጠው ይሄንኑ ነው፡ ምክንያቱም የአብዛኛዎች ምንባቦች ትኩረት የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውር፣ የአየር ንብረትና የአካባቢ ብክለት፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር …የመሳሰሉት ናቸው፡ እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች ተማሪዎቹ፤ ካሉበት የእድሜ እና የክፍል ደረጃ አንጻር ትኩረት ሰጥተው መከታተል ፍላጎት እንደሌላቸው በክፍል ምልከታውም ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል ፡፡

### 4.2.4 ከተማሪዎች የእለት ከእለት ገጠመኝ ጋር ያላቸው ቅርበት

ማዳመጥን በማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች አንድን ነገር በጥሞና እንዲያዳምጡ የሚቀርቡት ርዕሰ ጉዳዮች ለተማሪዎች ቅርብ ቢሆኑ እንደሚመረጥ በምዕራፍ ሁለት ቀርቧል፡፡ ይህም የሚሆንበት ዋነኛ ምክንያት ተማሪዎች የሚያዳምጡትን ነገር ከራሳቸው የህይወት ገጠመኝ ጋር በተያያዘ ሚሊኩ የሚቀርብላቸውን ምንባብ አትኩሮት ሰጥተው መከታተል ይችላሉ፡፡ይህ ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ የማዳመጥ ክሂላቸውን ሊያዳብርላቸው ይችላል፡፡ ይህን ሐሳብ ከግምት በማስገባት ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ማዳመጥን ለማስተማር በመምህሩ

ማምሪያ የቀረቡት ምንባቦች ላይ የሰነድ ፍተሻ በሚደረግበት ወቅት ለሚረዳት እንደተቻለው አብዛኛዎቹ ምንባቦች ከተማሪዎቹ ህይወትና የእለት ከዕለት ገጠመኝ ጋር ያላቸው ቅርበት አነስተኛ ነው፡ ለማስተማሪያነት ከቀረቡት አሰር ምንባቦች ውስጥ በተሻለ ሜልኩ ከተማሪዎቹ የዕለት ከዕለት ገጠመኝ ጋር ቀረቤታ ያለቸው ርዕሶች <<ቅርሶች በኢትዮጵያ>> እና <<ሰላምን ፍለጋ>> የሚሉት ናቸው ፡፡ ይህም ማለት ለተማሪዎች ህይወት ቅርበት ያላቸው ሆነው የተገኙት 20% የሚሆኑት ብቻ ናቸው፡

ማዳመጥን ለማስተማር የምንገለግልባቸው ጽሁፎች ተማሪዎች የእውኑን አለም የሚያገኙአቸው ጽሁፎችን በቀጥታ ወደ ክፍል ይዞ በመግባት ማስተማር የተሻለ እንደሆነ Underwood (1994፣ 98) ይገልጻሉ፡፡ ይህም ተማሪዎች በክፍል ያዳመጡትን ከክፍል ውጪም በሬድዮ፣ቴሌቭዥን … ሲነገር ለማስማት እንዲጓጉ ስለሚያደርጋቸው የማድመጥ ትምህርቱን በክፍል ውስጥ ብቻ ተተግብሮ እንዳይቀር ከፍተኛ እገዛ ይኖረዋል፡፡ ይህን አስሜልክቶ ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ማዳመጥን ለማስተማር ከቀረቡት ጽሁፎች ውስጥ በክፍል ያዳመጡትን ከክፍል ውጪም ለመተግበር የሚችላቸው <<ሰላምን ፍለጋ>> በሜል ርዕስ የቀረበው ጽሁፍ ነው፡ይህ ጽሁፍ ተማሪዎቹ በቤትም ሆነ ከቤት ወጪ በአብዛኛው ይሰሟታል ፡፡ ባሉት አጋጣሚዎች ሁሉ ሰዎች ምኞታቸውን ሲገልፁ ሲመርቁና ሲማራረቁ ያስተውላሉ፡፡እነሱም ለሰላም የድረሻቸውን መወጣት እንዳለባቸው የስገነዝባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ከሰነድ ምርማራው የተገኘው ውጤት እንደሚያስረዳው ክህሎቱን ለማስተማር የቀረቡት ጽሁፎች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን በውጪ እያዳማጡ እንዲተገብሩ ብዙም የሚያበረታቱ አይደሉም፡ ይህን አስሜልክቶ ለማምህራን የቀረበውን ማጠይቅ ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዠ 5 ማዳመጥን ለማስተማር የቀረቡ ምንባቦች ከተማሪዎች የዕለት ገጠመኝ እና ከእውኑ አለም ጋር ያላቸው ቅርበት

| | ማጠይቆች | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
|---|---|---|---|
| 1 | ክህሎቱን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች ከተማሪዎች የዕለት ዕለት ገጠመኝ ጋር ያላቸው ቅርበት | | |
| | 2 በጣም እስማማለሁ | - | - |
| | 2 እስማማለሁ | 4 | 22.2 |
| | 3 አልስማማም | 4 | 444.4 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | 3 | 33.3 |
| | | | |
| 2 | ለማስተማሪያነት የቀረቡት ጽሁፎች የእውኑን | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | አለም የሚያንጸባርቁ መሆናቸው | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | - | - |
| | 2 እስማማለሁ | 1 | 11.1 |
| | 3 አልስማማም | 5 | 56 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | 3 | 33.3 |

ከሰንጠረዥ 5 የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ማዳመጥን ለማስተማሪያነት የተዘጋጁት ምንባቦች ከተማሪዎቹ የእለት ከእለት ገጠመኝ ጋር ያላቸውን ቅርበት በተመለከተ ለመምህራን ለቀረበው ጥያቄ 44.4% የሚሆኑት እንደሚይስማሙ እና 33.3% የሚሆኑት ደግሞ ፈጽሞ እንደማይስማሙ የገለጹ ሲሆን 22.2% የሚሆኑት መምህራን ደግሞ ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ የዕለት ከእለት ገጠመኝ ጋር ቅርበት አላቸው በሚለው ሀሳብ እንደሚስማሙ ገልጸዋል፡፡ የአብዛኛዎቹ መምህራን ምላሽ እንደሚያሳየው እንዲሁም በሰነድ ፍተሻው ውጤት እንደሚያሳየው ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ የዕለት ከዕለት ገጠመኝ ጋር ያላቸው ግንኙነት አናሳ ነው፡፡

ማዳመጥን ለማስተማሪያነት የቀረቡት ምንባቦች የእውኑን አለም የሚያንጸባርቁ ስለመሆናቸው ለቀረበው ጥያቄ 56% የሚሆኑት እንደማይስማሙ እና 33.3% የሚሆኑት ደግሞ ፈጽሞ እንደማይስማሙ የገለጹ ሲሆን 11.1 % የእውኑን አለም ለማንጸባረቅ ይረዳል በሚለው ሀሳብ መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ለመምህራን ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ማዳመጥን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦች፣ ተማሪዎች በክፍል የተማሩትን ከክፍል ውጪ እንዲያንጸባርቁ የሚያበረታቱ አይደሉም፡

## 4.2.5 ስዕላዊ መገለጫ ስለመያዛቸው

ማዳመጥን ለማስተማር የሚዘጋጁ ምንባቦችን ከስእላዊ መገለጫ ጋር ተጣምረው መቅረባቸው መልካም ነው፡፡በተለይ ለማዳመጥ የተመረጡት ርዕሰ ጉዳዮች ከዕለት ዕለት ገጠመኞቻቸው ጋር አብረው የሚይሄዱ ከሆነ ስለሚያዳምጡት ነገር ተጨባጭ የሆነ ምስል እንዲኖራቸው እንዲሁም ለማዳመጥ የቀረበላቸውን ርዕሰ ጉዳይ በንቃት ለመከታተል ያስችላቸዋል ፡፡ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ማዳመጥ ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች አስፈላጊ ስዕላዊ መገለጫዎችን ማካተታቸውን ለማረጋገጥ የተደረገው የሰነድ ፍተሻ እንደሚያሳየው ማዳመጥን ለማስተማር የቀረቡትን ምንባቦች ተጨባጭ ለማድረግ የቀረቡ ስዕላዊ መገለጫዎች አሉ፡፡ ሆኖም ከአስሩ ክህሎቱን ለማዳበር ከተዘጋጁት ምንባቦች <<ቅርሶች በኢትዮጵያ >>እና<<ዶክተር ካትሪን ሀምሊን>> የሚሉት ብቻ የተሻለ ስዕላዊ መገለጫዎች የቀረበ ሲሆን ቀሪዎቹና አብዛኞቹ ምንባቦች ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት የሚያግዙ አይደሉም፡ ምንባቦቹ ተመጣጣኝ የሆነ ስዕላዊ መገለጫ አለመያዛቸው ለሚያዳምጡት ጽሁፍ ማስጠት የሚገባቸውን ትኩረት ይቀንሰዋል ፡፡ይህን አስመልክቶ ለመምህራን <<በመምህሩ መምሪያ በቀረቡት ምንባቦችና በተማሪው መጽሐፍ በተዘጋጁት ከምንባብ የወጡ መልመጃዎች

አዳምጦ የሚረዳት ክሂልን ለማስተማር የሚያስቸግሩ ነገሮች አሉ? ለሚለው ጥያቄ እንደ አስቸጋሪ ሁኔታ ከተገለጹት ነገሮች አንዱ የስዕላዊ መግለጫ ነው፡፡ለምሳሌ ''ለሁሉም ጊዜ አለው''የሚለው ጽሁፍ ከመቅረቡ በፊት ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ ላይ ገጽ 145 <<3- ስዕሉን አይታችሁ የተረዳችሁትን ነገር ግለፁ?>> የሚል ጥያቄ ቀርቧል፡፡ለዚህ ጥያቄ ተማሪዎች የተሻለ ማብራሪያ ማስጠት እንዲችሉ አሁን ከቀረበው ት/ቤትን ብቻ ከሚያሳይ ስእል ይልቅ የሚጫወቱ ተማሪዎች ፣ በቤተ-መፅሐፍ ተቀምጠው የሚያጠኑ ተማሪዎች ፣የሚማገቡ ተማሪዎችን ፣እንዲሁም በክፍል ውስጥ ተቀምጠው የሚማሩ ተማዎች በስእሉ ቢካተት የተሻለ ይሆናል፡፡ ፤ እንዲሁም ስዕሉን ተመልክተው የገለጹት በጽሁፉ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርበውን ምንባብ የማዳመጥ ፍላጎት ሊያድርባቸው ይችላል፡፡ሌላው <<የህፃናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ-ወጥ የሠዎች ዝውውር በከተማችን>>በሚል ርዕስ የቀረበው ለማዳመጥ ምንባብ በአጋዥነት የቀረበ ስዕል ሸመናን ብቻ የተጠቀመ ሲሆን ይህ በቂ አይደለም፡፡ምክንያቱም ርዕሱ በርካታ ስዕሎችን ማቅረብ የሚቻልበት እንደ የህፃናት ልመና ፣ የጉልበት ስራ ፤ የቤት ውስጥ ስራ….የማስሰሉትን ማሳየት ሲቻል ሸመናን የሚሰሩ ልጆች ብቻ ጉልበታቸው የሚበዘበዝ መሆኑን እንዲገነዘቡ ይገፋፋል፡፡

## 4.3 የመልመጃዎች የትምህርቱን አላማ የማሳካት ብቃት

የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚቀርቡ መልመጃዎች አቀራረብ የቅድመ ማዳመጥ ፣የማዳመጥ ጊዜና የድህረ ማዳመጥ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንዲሆን የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ማዳመጥ ለማስተማር የቀረቡት አስሩም ምንባቦች የቅድመ ማዳመጥ ፣ የማዳመጥ ጊዜና የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን አካተዋል፡፡ የመልመጃዎቹ አቀራረብ እንዴት እንደሆነ፣መልመጃዎች የሚቀርቡበትን አላማ ማሳከት በሚያስችል መልኩ ቀርበዋል ? ለሚለው ጥያቄ ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

### 1 ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች አቀራረብ

የቅድመ ማዳመጥ ጊዜ መካሄድ ያለባቸው ክንዋኔዎች በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው የማዳመጥ ፍላጎትን ማነሳሳተ ፣ ወደ ተዘጋጀላቸው ጽሁፍ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ እንዲሁም ለማዳመጥ በተዘጋጀላቸው ጽሁፍ ውስጥ ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ እንደሚችሉ እንዲገምቱ ማስቻል ነው ፡፡ይህን አላማ ለማሳካት የሚወጡ የቅድመ ማዳመጥ ጥቄዎችች ስለ ርዕሱ መገመት የሚያስችሉ ፣ውይይት ለመክፈት አመቺነት ያላቸው ፣ተማሪዎች የማድመጥ ፍላጎት እንዲያድርባቸው የሚያስችሉ፣ አዳዲስ ቃላትን ለማወቅና የሚያዳምጡበትን ምክንያት እንዲያውቁ የሚያስችሉ ጥያቄዎች መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

በመሆኑም ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ማዳመጥን ለማስተማር በመምህሩ መምሪያ ለቀረቡት ምንባቦች የተዘጋጁት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎ ምንባቡ ከመነበቡ በፊት በፊት መቅረባቸው ብቻ ሳይሆን አላማውን ማሳረት ያደረጉ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት በተደረገው የሰነድ ፍተሻ የቅድመ

ማዳመጥ ጥያቄዎቹ በአብዛኛው ትኩረታቸው የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ ነው፡ የተወሰኑት ደግሞ የምንባቡን ሀሳብ ማግመት ላይ ያተኩራሉ፡፡ለማስረጃነት የተወሰኑትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ገጽ66 <<የህዝብ ቁጥር ሚጨምር እንደ ሜልካም አጋጣሚ>>.

ቅድመ ማዳመጥ ፡- << የምንባቡን ሀሳብ ማግመት >> ለምሳሌ

1. የሕዝብ ብዛት መኖር ለአንድ ሀገር ምን ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

2. የሕዝብ ሀብትና የሀገር ሀብት ተመጣጣኝ ካልሆነ በሀገር ላይ ምን ጉዳት የሚያስከትል ይመስላኋል?

3 .ርእሱንና ስዕሉን ተሜልክታችሁ ምን ምን ጉዳዮች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ገጽ 81 <<የምድራችን ጀግና>>

ቅድመ ማዳመጥ ፡- <<የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ>> ለምሳሌ

1. በረሀማ ት ማለት ምን ማለት ይመስላቸዋል?

2. እፅዋትንና የሠው ልጅ ሕይወት የሚያገናኛቸው ምን ይመስላችኋል?

ገጽ 2. <<ሰው ለስራ>>

ቅድመ ማዳመጥ ፡- <<የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ>> ለምሳሌ

ለ. የስራ ሥነ -ምግባራትንዘርዝሩ፡፡

ገጽ 48 <<የሕይወት ቅዳጆች>>

ቅድመ ማዳመጥ፡ - <<የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ>> ለምሳሌ

1. በህይወታችሁ የማትረሱት ገጠሜኝ ካለ እስኪ ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡

ገጽ 97 <<የህፃናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውር በከተማችን >>

ቅድመ ማዳመጥ ፡- የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ ለምሳሌ

1. ስለ ሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነት የምታውቁትን ተናገሩ?

3. አንዳንድ ወላጆች ለሕፃናት የህገ ወጥ ዝውውር አስተዋፅኦ የሚያደርጉት በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ገጽ 112. <<ሰላምን ፍለጋ>>

ቅድመ ማዳመጥ ፡- የቀደመ እውቀትን መገመት ለምሳሌ

1 . ሰላምን ፈልጎ ማግኘት የሚቻል የሚመስላችኋል? እንዴት?

ገጽ 66 <<የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደ ሚልካም አጋጣሚ>>

ቅድመ ማዳመጥ ፡-<<የምንባቡን ሀሳብ መገመት >> ለምሳሌ

3. ርእሱንና ስእሉን ተመልክታችሁ ምን ምን ጉዳዮች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ገጽ 145 <<ለሁሉም ጊዜ አለው>>

ቅድመ ማዳመጥ ፡-<< ከርዕስ ተነስቶ የተውኔትን ሀሳብ መገመት>>

1.<<ለሁሉም ጊዜ አለው>> በሚል ርእስ በተፃፈ ተውኔት ምን ምን ርእሰ ጉዳዮች የሚዳሰሱ ይመስላችኋል?

ከላይ የቀረበው ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹ ከማዳመጥ በፊት ከመቅረባቸው ውጪ ትኩረት ተደርጎባቸው የትምህርቱን አላማ የሚያሳኩ ሆነው አልተገኙም፡አነዚህን ለቅድመ ማዳመጥ የቀረቡ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት ማነሳሳትና ስለሚያዳምጡት ምንባብ ግንዛቤው ኖሯቸው ለማዳመጥ እንዲዘጋጉ ማድረግ አስቸጋሪ ነው፡

## 2 የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች አቀራረብ

በማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ጥያቄዎች አላማ ዋና ዋና ሚእክቶችን እንዲረዱ ማስቻልና የአዳምጦ መረዳት ግንዛቤያቸውን ከፍ ማድረግ እንደሆነ በምዕረፍ ሁለት ተጠቅሷል፡፡ በሚሆኑም በዚህ ክፍል የሚቀርቡ ጥያቄዎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለማለየት ፣የምንባቡን አካሄድ ለማወቅ ፣ ጅምር ሀሳቦችን ለማሟላት ፣ ሰዋሰውና ቃላትን ለማስተማር ፣ስህተቶችን ለማረምና የተናጋሪውን ስሜት ለመረዳት የሚያስችሉ መሆን እንዳለባቸው ምሁራኑ ይገልጻሉ፡፡ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች አብዛኛው ተማሪ ሊመልሳቸው የሚችለው ያልረዘሙ ፣ የእውነት ሐሰት እና የምርጫ ጥያቄዎች መሆን እንደሚኖርባቸው ምሁራኑ አክለው ያስረዳሉ፡፡

በስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው ፡፡

- ✓ ህፃናትን ለህገ ወጥ ዝውውርና ለጉልበት ብዝበዛ የሚዳርገቸው ምክንያቶች ምን ምን ይመስኋል?
- ✓ ሠለሞን ቤት ውስጥ አሉ ተብለው ከተዘረዘሩት ቁሳቁሶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡

በሠለሞን ቤት ውስጥ በማዳማዳመጥ ወቅት የሚሞላስ የተዘረዘሩ ቁሳቁሶች የሉም ፡፡ይህ ጥያቄ ወይም በድህረ ማዳመጥ አልያም ጭራሹንም መቅረብ አይኖርበትም፡ ስለዚህ ይህ ጥያቄ አግባብነት የሌለው ነው፡

- ✓ ገጽ 50 ባልተሟቻቸ ሁኔታ የሚወለዱ ልጆች በሀገር ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ይመስላችኋል?
- ✓ ገጽ 61 የተፈጥሮ ሀብት ማጠበቅና መንከባከብ ምን ዓይነት ጠቀሜታ የሚኖረው ይመስላኋል?
- ✓ ገጽ 84 ሰላም በአንድ ወገን ጥረት እውን የሚሆን ይመስላኋል?
- ✓ ገጽ 103 ደኖች ያለአግባብ የሚጨፈጨፉ ከሆነ Type equation here.ምን የሚከሰት ይመስላኋል?
- ✓ ገጽ 117 ማትያስ የሰራው ስራ ተገቢ ነው ትላላችሁ? እንዴት?

እነ ዚህ ተማሪዎች ምንባቡን እያዳመጡ እንዲሞሏሏቸው የቀረቡት ጥያቄዎች የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች መመሪያን የተከተሉ አይደሉም ፡፡ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች የሚቀርቡበትን አላማ የሚያሳኩ ሆነው አልተገኙም፡አብዛኛዎቹ ትእዛዞች ተማሪዎች የሚመስላቸውን እና የሚሰማቸውን ነገሮች እንዲዘረዝሩ የሚጠይቁ ናቸው፡ይህ ደግሞ ከቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ ያድርገዋል፡፡ይህን ማስሉ ትእዛዝ ሙሉ ትኩረትን ምንባብ ላይ አድርጎ ለማከታተል አይጋብዝም ፡፡ ጥያቄዎቹ ተጨባጭ ስላልሆኑም መምህራን ተማሪዎቹ እያዳመጡ እንደነበር ለማከታተል አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል ፡፡ የቀረቡትን አይነት ጥያቄዎችን በምንባብ ሂደት ውስጥ ምላሽ ማስጠት ከባድ ነው ፡፡ ከስነድ ፍተሻ የተገኘውን ሚረጃ በምዕራፍ ሁለት ከቀረበው ንድፈ ሀሳብ ጋር በማቀናጀት እንደ አትኚዋ አስተሳሰብ ለማዳመጥ ጊዜ የቀረቡት ሚልመጃዎች ሁሉም አላማውን ማሳረት ያደረጉ አይደሉም፡

የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች አቀራረብ

የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ዋና አላማ ያዳመጡትን ሚላስ ብለው እንዲቃኙ እና የቀረበላቸውን ምንባብ በአግባቡ ማከታተላቸውን ለሚፈተሽ ማስቻል ነው፡ በድህረ ማዳመጥ ወቅት መቅረብ ያለባቸው ጥያቄዎች በጥንድ ፣ በቡድን በሚሆን እንዲወያዩ ፣እንዲከራከሩ ለሚድረግ የሚያስችሉ ፣ ማጠቃለያ ለሚጻፍ የሚያስችሉ፤ የተናጋሪውን አማካከት ለማለየት የሚስችሉ መሆን እንዳለባቸው የተለያዩ ምሁራን እንደሚገልጹ በምእራፍ ሁለት ቀርቧል፡፡

በስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች የአብዛኛዎቹ ትኩረት <<የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ ማሳረት በቃላችሁ ሚልሱ>> የሚሉ ናቸው፡ምንባቡ ለይ ማሳረት ያደረጉ አጭጭር ሚልሶችን እንዲሰጡ የሚያበረታቱ ናቸው ፡፡ለሚጻፍ ፣እርስ በርስ ለመወያየት የሚያስችል አይነት አቀራረብ ያላቸው አይደሉም፡ ነገር ግን በቅድመ ማዳመጥ እና በማዳመጥ ጊዜ ከቀረቡት ሚልመጃዎች በተሻለ ሁኔታ አላማውን ለማሳከት የሚያስችሉ ናቸው ፡፡የቀረበላቸውን ምንባብ

በአግባቡ ማከታተል አለማከታተላቸውን ለሚተሸ የሚስችሉ ፣እንዲሁም ያዳማጡትን ማሳረት አድርገው የራሳቸውን አስተሳሰብ እንዲገልጹ የሚያበረታቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል ፡፤ ለምሳሌ

ገጽ 3.ስራን ማስራት እንዴት ራስን ፣ ቤተሰብን ፣ ሀገርንና ዓለምን እንደሚቀይር አብራሩ፡፡

ገጽ 17 ባህላዊ ቅርስ ማለት ምን ማለት ነው?

ገጽ 67 ለድህነት መባባስ በምክንያትነት የተጠቀሰው ምንድን ነው?

ገጽ 82 የምንባቡ አጠቃላይ ሐሳብ ምንድነው?

ገጽ 97 የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛና ህገ ወጥ ዝውውር በሕፃናቱ ላይ የሚያስከትሏቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች ምን ምን ናቸው?

ከሰነድ ፍተሻው የተገኘውን መረጃ ማሳረት በማድረግ በድህረ ማድመጥ ወቅት የቀረቡት ጥያቄዎች አላማውን ከማሳካት አንጻር የተሻሉ ናቸው ፡፡ ማዳመጥን ለማስተማር የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ፣የማዳመጥ ጊዜን የድህረ ማዳመጥ ሜለመጃዎችን አስሜልክቶ ለመምህራን ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 6 ማዳመጥን ለማስተማር ከቀረቡት ምንባቦች የወጡት ሜለመጃዎች የጽሁፉን ሜልዕክት እንዲገነዘቡ ማስቻላቸውና ለትምህርት አሰጣጥ አመቺ መሆናቸውን በተማለከተ

| | ማጠይቆች | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
|---|---|---|---|
| 1 | የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የሚቀርቡለትን አላማ ለማሳካት ያስችላሉ | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | - | - |
| | 2 እስማማለሁ | 7 | 67 |
| | 3 አልስማማም | 1 | 11.1 |
| | 4 ፈጽሞ አልስማማም | 1 | 11.1 |
| 2 | በማዳመጥ ሂደት የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች እየተነበበላቸው ያለውን ምንባብ በትኩረት እየተከታተለ እንደነበር ለማከታተል ያስችላሉ | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | 1 | 11.1 |
| | 2 እስማማለሁ | 3 | 33.3 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 3 አልስማማም | 3 | 33.3 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | 2 | 22.2 |
| 3 | የድህረ ማዳመጥ ሜልመጃዎች ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ምንባብ በአግባቡ መከታተላቸውን ለሚፈተሽ ያስችላሉ | | |
| | 1 በጣም እስማማለሁ | 3 | 33.3 |
| | 2 እስማማለሁ | 5 | 56 |
| | 3 አልስማማም | 1 | 11.1 |
| | 4 ፍጹም አልስማማም | | |

ከሰንጠረዥ 6 የተገኘው መረጃ እንደሚያሚለክተው የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹ የቀረቡበትን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ስለሚሆናቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ 67% የሚሆኑት መምህራን በሀሳቡ እንደሚስማሙ የገለጹ ሲሆን 11.1% የሚሆኑት ፈጽሞ አልስማማም እና 11.1% የሚሆኑት በሀሳቡ እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡አብዛኛዎቹ መምህራን የሰጡት ምላሽ በሰነድ ፍተሻው ከተገኘው ምላሽ ጋር የሚያስማማ አይደለም፡

በማዳመጥ ሂደት ለተማሪዎቹ የቀረቡት ጥያቄዎች እየተነበበላቸው ያለውን ምንባብ በትኩረት እያዳመጡ መሆናቸውን ለመከታተል አመቺ ስለሚሆናቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ 11.1% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ እና 33.3% የሚሆኑት ደግሞ እንደሚስማሙ የገለጹ ሲሆን 33.3% የሚሆኑት እንደማይስማሙ እና 22.2% የሚሆኑት ደግሞ ፈጽሞ እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ የመምህራን አማለካከት አሉታዊና አዎንታዊ ነው፡፡ የሰነድ ፍተሻው የሚያሚለክተው ደግሞ ጥያቄዎቹ አመቺ አለመሆናቸውን ነው፡

የድህረ ማዳመጥ ሜልመጃዎቹ ተማሪዎች ለማዳመጥ የቀረበላቸውን ምንባብ በአግባቡ እያዳመጡ እንደነበር ለሚፈተሽ የሚያስችሉ ስለሚሆናቸው ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ 56% የሚሆኑት እንደሚስማሙ እና 33.3% የሚሆኑት ደግሞ በጣም እንደሚስማሙ የገለጹ ሲሆን 11.1% የሚሆኑት ደግሞ በቀረበው ሐሳብ እንደማይስማሙ ገልጸዋል ፡፡ከአብዛኛው መምህር የተገኘው ምላሽ እንዲሁም የሰነድ ማስረጃውን በማከተት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹ አቀራረብ ከቀረበለት አላማ አንጻር የተሻለ ነው፡

## 4.4 ምንባቦችና ሜልመጃዎች ክህሎቱን ለማስተማር ያላቸው አመቺነት

ማዳመጥን ለማስተማር የሚመረጡ ምንባቦች ለሙተግበር በሚያመች ሜልኩ ወይም ትምህርቱን ለማስጠት አመቺ በሆነ መንግድ መዘጋጀት እንዳለባቸው በምእራፍ ሁለት ተገልጸዋል፡፡ ምንባቦቹ የተማሪዎቹን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ፣ ከአንዱ አንቀጽ ወደሌላው በሚሸጋገሩበት ወቅት የተማሪዎችን ሀሳቦቹን አቀናጅቶ ማዳመጥ ችሎታ ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል ፡፡ ሜልመጃዎቹም የቀረቡበትን አላማ ማሳካት የሚቻሉት

፣በጣም ያልቀለሉ ወይም በጣም ያልከበዱ ሲሆኑ ነው፡ይህን አስመልክቶ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማስተማር በመምህሩ መምሪያ የቀረቡት ምንባቦች እና ከምንባቦቹ የወጡ መልመጃዎች ክህሎቱን ለማስተማር አመቺ ናቸው ? በሚል ለቀረበው ጥያቄ 67% የሚሆኑት መምህራን፡ -

የምንባቦቹ ለትምህርት አሰጣጡ አመቺ ከሚሆናቸው አንጻር ሲታይ አብዛኛዎቹ ምንባቦች ስነጽሁፋዊ ይዘት ስላላቸው ለማስተማር አመቺ የሆኑ ቢመስሉም ለአንብቦ ሚረዳት ከቀረቡት ምንባቦች ጋር በሀሳብ ስለሚስማሙ ተማሪዎቹ አስቀድመው ስለምን ለነገር እንደሆነ ይረዳሉ፤ ስለሆነም አዲስ ሚረጃ ስለማይሆንባቸው ለሚቀርበው ምንባብ ትኩረት ሲሰጡ አይታይም ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች እያዳመጡ ማስታወሻ እንዲይዙ መምሪያ ቢሰጣቸውም ሲይዙ አይታይም፡ ስለዚህ ለማዳመጥ የቀረቡት ምንባቦች ለአንብቦ ሚረዳት ከቀረቡት የተለዩ ስላልሆኑ ብዙም ሳቢ ሆነው እኛንም ለማስተማር ተማሪዎቹንም ለመማር የሚያነሳሱ አይደሉም ፡፡ ከምንባብ የወጡት መልመጃዎች ግን ክህሎቱን ለማስተማር አስቸጋሪ አይደሉም ፡፡ ነገር ግን መልመጃዎቹን ለማሰራት የተሰጠው ጊዜ በቂ አይደለም ፤ አብዛኛውን ጊዜ ምንባቡን አስደምጠን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ለማሰራት ጊዜ አይኖርም ፡፡

በማለት መልስ የሰጡ ሲሆን 44.4% የሚሆኑት መምህራን ደግሞ << ማዳመጥን ለማስተማር የተበደበው ጊዜ በቂ አለመሆኑ እንጂ ክህሎቱን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦችም ሆኑ ከምንባብ የወጡ መልመጃዎች ትምህርቱን ለማስጠት አስቸጋሪ አይመስሉንም>> በማለት መልስ ሰጥተዋል ፡፡

ማዳመጥን ለማስተማር የቀረቡት ምንባቦችን በተማለከተ የሰነድ ፍተሻውም አብዛኛዎቹ መምህራን ያላቸውን አማላካከት የሚደግፍ መሆኑ ከዚህ በፊት በቀረቡት ሚረጃዎች ለመግለጽ ተሞክሯል ፡፡ በመልመጃዎቹ አመቺነት ዙሪያ ግን ከመምህራን የተገኘው ምላሽ በሰነድ ፍተሻው በ1.1.9 ከቀረበው ማስረጃ ጋር የሚስማማ አይደለም ፡፡ ክህሎቱን ለማስተማር የተሰጠውን ጊዜ አስመልክቶ ከመምህራን የተሰተው አስተያየት በክፍል ምልከታው ወቅትም ለሚረጋገጥ እንደተቻለው ተማሪዎችን በማሰተፍ ከምንባብ የወጡ መልመጃዎችን ለማሰራት የተመደበው ጊዜ በቂ አይደለም ፡፡ ምክንያቱም ለአብዛኛዎቹ ማዳመጥን ለማስተማር የተሰጠው ጊዜ አስራ አምስት ደቂቃ ብቻ ነው፡

## 4.5 ከምልከታ የተገኙ ምላሾች ትንተና

### 4.5.1መምህራን የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ያላቸው ተነሳሽነት

ሰንጠረዥ 7 መምህራን ማዳመጥን ለማስተማር በተዘጋጁት ምንባቦችና ከምንባብ በወጡ መልመጃዎች ክህሎቱን ለማስተማር ያላቸውን ተነሳሽነት ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ ሚረጃ

| ተ.ቁ | የምልከታ ማካታተያ ነጥቦች | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የእለቱን የማዳመጥ ትምህርት በተመለከተ መደረግ ያለበትን ክንውን የሚያሳይ ዕለታዊ እቅድ ማዘጋጀቱ | | 2(11.1%) | 6(33.3%) | 10(56%) |
| 2 | የትምህርቱ አላማ ምን እንደሆነ ለተማሪዎቹ በግልጽ መቅረቡ | | 2(11.1%) | 6(33.3%) | 10(56%) |
| 3 | ምንባቡ ለተማሪዎች በሚቀርብበት ጊዜ የመምህሩ ድምጽ በጥራት የመደመጥ ሁኔታ | 10(56%) | 8(44.4%) | | |
| 4 | የማዳመጥ ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ማስተማሪያ መሳሪዎችን ተጠቅሞ የማስተማር ሁኔታ | | | | 18(100%) |

ከሰንጠረዥ 7 የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ለአስራ ስምንት ተከታታይ ጊዜያት በተደረገ ምልከታ መምህራን የማዳመጥ ትምህርትን አስመልክቶ ዝርዝር ክንውንን የሚያሳይ ዕለታዊ ዕቅድ አውጥተው የነበረው 11.1% ከፍተኛ ፣33.3 በመቶ መካከለኛ እና 56 % የሚሆነው ደግሞ ዝቅተኛ እንደነበር በምልከታው ታውቋል፡፡ከተገኘው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው አብዛኛው መምህር ለማዳመጥ ትምህርቱ ትኩረት ሰጥቶ ክንውኑን የሚያሳይ ዕለታዊ እቅድ እንደሚያዘጋጅ ነው፡

የማዳመጥ ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት የትምህርቱ አላማ ምን እንደሆነ የተገለጸበት ሁኔታ 11.1 በመቶ ከፍተኛ 33.3% የሚሆኑት ደግሞ መካከለኛ አተገባበር የነበራቸው ሲሆን 56%ለሆኑ የምልከታ ጊዜያት ደግሞ የትምህረቱን አለማ ለተማሪዎች የማስገንዘብ ሁኔታ ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህ መረጃ እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉ ጽሁፉ ለምን እንደሚበብላቸው ማሳወቅ ተገቢ ነው፤ ሆኖም አብዛኛዎቹ መምህራን ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥተው አላማውን አላሳወቁም፡

የማዳመጥ ትምህርትን ለማስተማር በሚደረግ ዝግጅት ወቀት ተማሪዎች ስለሚያዳምጡት ምንባብ ምስላዊ መረጃ እንዲኖራቸው እና ስእሉን ተመልክተው ስለምን ሊያዳምጡ እንደሆነ ለማወቅ ጉጉት እንዲያድርባቸው ስዕል ፣ ካርታ ፣ርእሰ ጉዳዩን አስመልክቶ የተቀረጹ ስራዎችን በማጠቀም ትምህርቱን መቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ተግባር በመጽሐፎቹ ትኩረት ተሰጥቶት እንዳልቀረበ ከዚህ በፊት ቀርቧል ፡፡ ሆኖም መምህራን በራሳቸው ተነሳሽነት ማዳማጡን የሚያግዙ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን አዘጋጅተው ያስተምሩ እንደሆነ ለማወቅ

ምልከታ ተደርጓል ፡፡ ከምልከታው የተገኘው መረጃ እንደሚያሚለክተው በአስራ ስምንቱም የምልከታ ጊዜ ምንም የቀረበ ማስተማሪያ መሳሪያ የለም ፡፡ ይህም የሚያሚለክተው መምህራኑ ለማዳመጥ ትምህርቱ ትኩረት ሰጥተውና አስቀድመው ተዘጋጅተው በመምህሩ መምሪያ የቀረበውን ምንባብ የማስተማር ተነሳሽነት እንደሌላቸው ነው፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ

የመምህሩ መምሪያ አንዱ የማስተማሪያ መሳሪያ ነው ፡፡ስለሆነም በመመምህሩ መምሪያ ላይ የቀረቡትን ፣ ክንውኖች ማሰረት አድርገው ማዳመጥን ያስተምሩ እንደሆነ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኛዎቹ መምህራን፡ -

*የመምህሩ መምሪያ ላይ የቀረበውን አካሄድ ተከትሎ ለማስተማር የተሰጠው ጊዜ በቂ አይደለም፡ የማዳመጥ ትምህርቱ ከ<<መናገር >>ክሂል ጋር አብሮ የሚሰጥ ነው፤ ስለሆነም በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ሁለቱን ይዘቶች ለማስተማር በቂ ጊዜ አልተመደበም፡ ስለዚህ የመምህሩ መምሪያ የሚለውን ተከትሎ ትምህርቱን ማስጠት ካለው ጊዜ አንጻር አስቸጋሪ ነው፡*

በማለት ሚልስ የሰጡ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ

*የማዳመጥ ትምህርቱ የሚሰጠው በመምሪያ መፅሐፉ ላይ ከንባብ ትምህርት ጋር ተቀራራቢ በሚሆኑ በመምሪያ መጽሐፋቸው ላይ ሲያነቡት የነበረውን መረጃ ሚልሳችሁ እኔ ሳነብላችሁ አዳምጡ እንደማለት ስለሆነ ያን ያህል ትኩረት አንሰጠውም፡*

በማለት ሚልስ ሰጥተዋል

ምልከታው በተካሄደበት ወቅት ከነበሩት የትምህርት ርዕሶች አንዱ በአስረጂነት እንደሚከተለው ቀርቧል

ገጽ 96

አስረጂ የትምህርቱ ርዕስ፡ -

የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛና ሕገ ወጥ ዝውውር በከተማችን

ቅድመ ማዳመጥ

1. ስለ ሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነት የምታውቁትን ተናገሩ?

2.ሕገ ወጥ የህፃናት ዝውውር ሲባል ምን ማለት ይማስላቸወል?

3. አንዳንድ ወላጆች ለሕፃናት የህገ ወጥ ዝውውር አስተዋፅኦ የሚያደርጉት በምን ዓይነት መንገድ ነው?እንዴት?

4. ስዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ነገር አብራሩ፡፡

የማዳመጥ ጊዜ

- በህገ ወጥ መንገድ ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ የሚሰሙበቸው የስራ ማስኮች ምን ምን ናቸው ?

- ሕፃናትን ለሕገ ወጥ ዝውውርና ለጉልበት ብዝበዛ የሚዳርጓቸው ምክንያቶች ምን ምን ይመስሏችኋል?

ድህረ ማዳመጥ(አዳምጦ መረዳት)

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ካዳመጣችሁት ምንባብ በመነሳት ትክክለኛ መልስ ስጡ፡

1.ሕፃናትን በአቅማችሁ ማስራት አለባቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

2.ሕፃናትን ለጉልበት ብዝበዛና ለህገ ወጥ ዝውውር የሚዳርጉ መንስኤዎች ምን ምን ናቸው?

3.የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከተለያዩ ወንጀሎች ጋር ይያያዛል ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

4.የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛና ህገ ወጥ ዝውውር በሕፃናቱ ላይ የሚያስከትሏቸው አሉታዊ ተፅእኖዎች ምን ምን ናቸው?

5.ለህገ ወጥ ዝውውር የሚጋለጡ ሴት ሕፃናት ለተለያዩ ችግሮች የዳረጋሉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

6.ሕፃናት ከወላጆቻቸው መገኘት ያለባቸው ነገር ምንድነው?

7.የሕፃናት መብት ድንጋጌዎች ላይ የሰፈሩት ሀሳቦች ምንድናቸው?

ከላይ የቀረበው መረጃ መምህራኑ ከአንድ ክንውን ወደሚቀትለው ክንውን እንዴት ማሻገገር እንዳለባቸው የቅድመ ማዳመት እና የድህረ ማዳመጥ መልመጃዎችን በምን አይነት መልኩ መምህራም ማሰራት እንዳለባቸው መንገድ ያመላክታል ፡፡ ነገር ግን ለአያንዳንዱ ክንውን የሰጠው ሰአት የማዳመጥ ክሂልን በተገቢው መንገድ ለማስተማር እና ተማሪዎችን በበቂ ሁኔታ አሳትፎ የቀረበላቸውን ምንባብ በትክክል እያዳመጡ መሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም ፡፡

መምህራን ማዳመጥን ለማስተማር በመምህሩ መምሪያ የቀረቡትን ምንባቦች በትክክለኛ ድምጸት የማቅረብ ተነሳሽነታቸውን በተመለከተ የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው 56% ለሚሆኑ ክፍለ ጊዜያት መምህራኑ

ምንባቡን ለተማሪዎች ያቀረቡበት ድምጸት በጣም ከፍተኛ ነጥብ የሚያሰጥ ሲሆን 44.4% ለሚሆን የክፍል ምልከታ የመምህራኑ የድምጽ ሁኔታ ከፍተኛ ነጥብ ላይ የሚቀመጥ ነው፡፤

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያሳክቱት መምህራን ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁ ምንባቦችንና ከምንባብ የወጡ ማልመጃዎችን በመጠቀም ክህሎቱን በአግባብ የማስተማር ተነሳሽነታቸው መሻሻል የሚገባው ነው፡

## 4.5.2 የመምህራን የማዳመጥ ትምህርት አቀራረብ

መምህራን በመምህሩ መምሪያ ከቀረቡት ምናባቦች የወጡ ማልመጃዎች አላማቸው ምን እንደሆነና አላማቸውን ለማሳካት የሚረዱ ጥያቄዎች አቀራረብ እንዴት መሆን እንዳለበት ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ማልመጃዎቹን በክፍል ውስጥ እንዴት ተማሪዎችን እንዳሰሯቸው ሚፈተሸ አስፈላጊ ነው፡ በመሆኑም ከምልከታው የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፤

ሰንጠረዥ 8 የመምህራንን ከምንባብ የወጡ የማዳመጥ ክሂል ማልመጃዎች አቀራረብ ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በቅድመ ማዳመጥ ፣በማዳመጥ ሂደትና በድህረ ማዳመጥ ወቅት የሚቀርቡ ጥያቄዎች አላማቸው ምን እንደሆነ ለተማሪዎች ማቅረብን በተመለከተ | | | 3(17 %) | 15(83.3%) |
| 2 | በመምሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በአግባቡ ጠይቆ ምላሽ እንዲሰጡ የሚድረግ ሁኔታ | | 8(44.4%) | 6(33.3%) | 4(22.2%) |
| 3 | ለማዳመጥ የታቀደው ምንባብ ለተማሪዎቹ ከመቅረቡ በፊት እንዴት ማዳመጥ እንዳለባቸው ግልጽ መመሪያ የማስጠት ሁኔታ | 7(39%) | 5(28%) | 3(16.7%) | 3(16.7%) |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 4 | ተማሪዎች እየተነበበላቸው ያለውን ምንባብ በአግባቡ እየተከታተሉ መሆኑን ለማወቅ በየመካከሉ ጥያቄዎችን ለማቅረብ የነበረ ተነሳሽነት | | 3(17%) | 5(28%) | 10(56%) |
| 5 | ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ በአግባቡ ማከታተላቸውን ለማንዘብ ለቀረቡት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች የተሰጠ ግብረ መልስ | | 6(33.3%) | 4(22.2%) | 8(44.4%) |

የማዳመጥ ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎች እንዴት ማከታተል እንዳለባቸው ለተማሪዎች የተሰጠ መመሪያን በተመለከተ የተገኘው መረጃ 39% በጣም ከፍተኛ ፣28% ከፍተኛ ፣ 17% መካከለኛ እና 17% ደግሞ ዝቅተኛ አተገባበር ታይቷል ፡፡ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ለማዳመጥ ትምህርት የተዘጋጀውን ምንባብ ለተማሪዎች ከማቅረባቸው በፊት እንዴት ማዳመጥ እንዳለባቸው አጠቃላይ መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ አብዛኛዎቹ መምህራን ይሰጡ የነበረው መመሪያ የሚከተለውን ነው

> አሁን የምትማሩት ማዳመጥ ነው፡ የማነብላችሁ ምንባብ የሚገኘው ማስተማሪያ መጽሐፉ ላይ ነው፡ ምንባቡን ትኩረት በማስጠት ፀጥ ብላችሁ ተከታተሉ ፡፡ ከየምታዳምጡት ምንባብ ዋናዋና ነጥቦቹን ማስታወሻ እየያዛችሁ ተከታተሉ ፤ከዚያም ባዳመጣችሁት ምንባብ ማሰረት ለድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡

የሚል ነው፡ ነገር ግን መመሪያው ይህን አድርጉ ያንን አታድረጉ የሚል ሐሳብን የያዘ ሲሆን ለምን እንደሚያደርጉና ለምን እንደሚያድርጉ ከአላማው አንጻር በዝርዝር ስላልቀረበላቸው ለመመሪያው ተማሪዎች የሰጡት ትኩረት እምብዛም ነው፡በቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥ ሂደትና በድህረ ማዳመጥ ወቅት የሚቀርቡ ጥያቄዎች አላማቸው ምን እንደሆነ ለተማሪዎች የመቅረቡን ሁኔታ በተመለከተ የነበረው አተገባበር 17 በመቶ በሚሆኑት ምልከታዎች መካከለኛ 83.3% በሚሆኑት ምልከታዎች ደግሞ ዝቅተኛ ነበር ፡፡ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው የተወሰነ ድክመት የታየ ቢሆንም የመምህራን ትኩረት አጠቃላይ የትምህርቱን አላማ ለተማሪዎች መንገርን እንጂ መልስ እንዲሰጡባቸው የቀረቡላቸው የቅድመ ማዳመጥ ፣ የማዳመጥ ጊዜና ፣የድህረ ማዳመጥ መልመጃዎች አላማቸው ምን እንደሆነ አይገልጹላቸውም፡ ተማሪዎች የመልመጃዎቹ አላማ

አስቀድመው ማወቃቸው የሚቀርብላቸውን ምንባብ ትኩረት ሰጥተው ለማከታተል ያስችላቸዋል፡፡ የትምህርቱ አስፈላጊነት ምን እንደሆነ ም ለሚረዳት ያስችላቸዋል፡፡

ተማሪዎች ለቅድመ ማዳመጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በአግባቡ እንዲሰሩ መደረጋቸውን አስመልክቶ የተደረገው ምልከታ 44.4በመቶ ከፍተኛ ፣ 33.3 በመቶ መካከለኛ እና 22.2 በመቶ ደግሞ ዝቅተኛ ነበር፡፡ይህ መረጃ የሚያመለክተው ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በማሰራት ረገድ የመምህራኑ ተነሳሽነት የተሻለ እንደነበር ነው፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተራ ቁጥር 6 የቀረበውን መረጃ በተመለከተ ተማሪዎች እየቀረበላቸው ያለውን ምንባብ በአግባቡ እየተከታተሉ መሆኑን ለማወቅ የሚያነቡትን ምንባብ ገታ እያደረጉ ጥያቄዎችን የማቅረብ ተነሳሽነትን በተመለከተ 17%ከፍተኛ ፣ 28%መካከለኛ አቀራረብ የነበረ ሲሆን 56 በመቶ በሆኑት የምልከታ ጊዜያት በማዳመጥ ሂደት ጊዜ ጥያቄዎች አቀራረብ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚቀመጥ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ መምህራን ምንባቡን በቀጥታ ማንብበ እንጂ ተማሪዎቹ ከሚገበበው ምንባብ ጋር እንዲሆኑ ለማስቻል ያደረጉት ጥረት ዝቅተኛ ነው፡

ምንባቡ ከተነበበ በኋላ ለቀረቡት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች ለሚሰጡት ምላሽ ትክክለኛ መሆን አለመሆኑን እንዲያረጋግጡ ፤እንዲሁም ምንባቡ እየተነበበ በነበረበት ወቅት የተማሪዎቹ ትኩረት የሚገበበው ምንባብ ላይ እንደነበር የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን አቅርቦ ግብረ መልሳቸውስ ማስጠት ተገቢ ነው፡ ይህን አስመልክቶ በተራ ቁጥር 8 የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው 33% ከፍተኛ ፣22.2% መካከለኛ ሲሆን 44.4% ግብረ መልስ የማስጠታቸው ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡ ይህ መረጃ እንደሚያመለክተው መምህራን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን የማሰራት ሁኔታቸውም መሻሻል የሚገባው መሆኑን ነው፡

በአጠቃላይ መምህራን ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁ ምንባቦችና ከምንባብ የወጡ መልመጃዎችን ለተማሪዎች በምን መልኩ ማቅረብ እነሰዳለባቸው ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው መምህራኑ ያላቸው ግንዛቤ መሻሻል የሚገባው መሆኑን ነው ፡፡ ምክንያቱም ምንባቡን ለተማሪዎች በሚያቀርቡበት ጊዜ ተማሪዎች እንዲዳምጡ ለማድረግ ምንባብን ገታ እያደረጉ ጥያቄዎችን የማቅረብ ሁኔታቸው በአማኙ ዝቅተኛ ነው ፡፡ ከምንባብ የወጡ መልመጃዎች አላማ ምን እንደሆነ ለተማሪዎቹ ነግሮ ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ እንዲሁም ጥያቄዎችን የማሰራት ተነሳሽነታቸው ዝቅተኛ ስለሆን ይህ ሁኔታ ሊፈጠር የቻለበት ምክንያት ምንባቡም ሆነ ከምንባብ የወጡ መልመጃዎች ክህሎቱን ለማስተማር ያላቸውን ፋይዳ ፣ አላማቸው ምን እንደሆነ ካለሚረዳት የመጣ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማል፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ ጋር በተያያዘ << ማዳመጥን ለማስተማር ከተዘጋጁት ምንባቦች የወጡ መልመጃዎችን ለማሰራት የተመደበው ጊዜ በቂ ነው>> ለሚለው ጥያቄ መምህራን የሰጡት ምላሽ አዎንታዊም አሉታዊም አመለካከቶችን የያዘ ነው፡60 በመቶ የሚሆኑት መምህራን ፡-

ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ አንብቦ ጥያቄዎችን ለማሰራት የተመደበው ጊዜ በቂ ነው፡ ሆኖም ማዳመጥን በምናስተምርበት ክፍለ ጊዜ << መናገር>> አብረው ለተማሪዎች ይቀርባሉ ፤ሁለቱን ይዘቶች ለማስተማር በቂ ጊዜ አናገኝም እንጂ ክህሎቱን ለማስተማር በራሱ የተመደበው ጊዜ በቂ ነው፡

በማለት ሃሳ የሰጡ ሲሆን 40 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ

ክህሎቱን ለማስተማር የተመደበው ጊዜ በቂ አይደለም ፡፡ተማሪዎች ምንባቡን በማስተዋል እንዲያዳምጡ ምንባቡን በእርጋታ ማንበብ አለብን ፡፡ አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ መድገም ይኖርብናል ፤ይህን አድርገን ተማሪዎችን እያሳተፍን የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ለማሰራት የተመደበው ጊዜ በቂ አይደለም ፡አብዛኛውን ጊዜ ጥያቄዎቹን አሰርተን አንጨርስም፡

በማለት ሃሳ ሰጥተዋል

### 4.5.3 ተማሪዎች ለምንባቦችና ጥያቄዎች የሚሰጡት ትኩረት

ሰንጠረዥ 9 ተማሪዎች የማዳመጥ ትምህረትን ለማስተማር በመምህራን ለሚቀርብላቸው ምንባብ እና ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎች የሚሰጡትን ትኩረት ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች ከተነበበላቸው ምንባቦች ለወጡ ጥያቄዎችን ለማስራት የነበራቸው ተሳትፎ | | 3(17%) | 6(33.3%) | 9(50%) |
| 2 | ተማሪዎችች ምንባቡን በሚከታተሉበት ወቅት ያልገባቸው የቃላትና የሐረጋት ፍቺዎችን መዝግበው መምህራቸውን የመጠየቅ ተነሳሽነት | | | 3(17%) | 15(83.3%) |
| 3 | ተማሪዎች እየቀረበላቸው ያለውን ጽሁፍ እየተከታተሉ ማስታወሻ የመያዝ ሆኔታ | | | 6(33.3%) | 12(67%) |

ከሰንተረዥ 9 የተገኘው መረጃ እንደሚያሣየው በቅድመ ማዳመጥ ፤በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ ወቅት ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለማስጠት የነበረው ተሳትፎ በምልከታው ሶስት ክፍለ ጊዜያት ወይም 17% ከፍተኛ ፤ለስድስት ክፍለ ጊዜያት 33.3% መካከለኛ የነበረ ሲሆን የዘጠኙ ክፍለ ጊዜያት 50% ዝቅተኛ ነው ፡፡ ተማሪዎች ምንባቡን በሚከታተሉበት ወቅት ለሚረዳት አስቸጋሪ የሆኑባቸውን ቃላትና ሐረጋት መዝግቦ

ከመምህራቸው ጋር የመወያየት ሁኔታን አስመልክቶ ከተደረገው ምልከታ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው 17% መካከለኛ ሲሆን 83.3% ደግሞ ዝቅተኛ ነው፡ አብዛኛዎቹ መምህራን ምንባቡን ለተማሪዎች ከማቅረባቸው በፊት <<ምንባቡን በትኩረት እያዳመጣችሁ ማስታወሻ ያዙ >> የሚል መመሪያ ያስተላለፉ ቢሆንም ሰንጠረዥ 9 ተራ ቁጥር 3 ላይ የተመለከተው መረጃ መመሪያው ተግባራዊ መሆኑን አያመለክትም ፡፡ መረጃው የሚያመለክተው የተማሪዎቹ የሚነበብላቸውን ጽሁፍ እየተከታተሉ ማስታወሻ የሚያዝ ሁኔታ 33.3% መካከለኛ ሲሆን 67% ዝቅተኛ ነው፡

በአጠቃላይ ከሰንጠረዥ9 የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ማዳመጥን ለማስተማር ለቀረቡት ምንባቦችና ከምንባቦቹ ለወጡ መልመጃዎች ያላቸው በአግባቡ ለመከታተልና ለመልመጃዎች መልስ ለመስጠት የነበራቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ ነው፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓብይ አላማ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብን መፈተሽ ነው፡ የዚህ ምዕራፍ ዋና አላማ ከዚህ ዓብይ አላማ ስርም ለተነሱት አራት ንዑሳን አላማዎች እና አነሳሽ ምክንያት መልስ ማስጠት ነው፡ጥናቱም የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝቷል፡፡

ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ እንዲሁም ለተማሪዎቹ አዳዲስ መረጃን በማቀበል በትኩረት እንዲያዳምጡ ማድረግ ከማስቻላቸው አንጻር ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው ውጤት የሚያማለክተው ምንባቦቹ ላይ ክፍተት እንዳለ ነው ፡፡በሰነድ ፍተሻው እንደተረጋገጠው አብዛዎቹ ምንባቦች ከተማሪዎቹ የዕለት ከዕለት ገጠመኝ ጋር አብረው የማይሄዱና ለአንብቦ መረዳት ከተዘጋጁት ምንባቦች ጋር ተመሳሳይ ሀሳብን የያዙ ናቸው፡

ማዳመጥን ለማስተማር ከተዘጋጁት ምንባቦች የወጡ መልመጃዎች መልመጃዎቹ የሚቀርቡበትን አላማ ማሳካትን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ስለመሆናቸው ለማረጋጥ የተደረገው የሰነድ ፍተሻ እንደሚያማለክተው የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹ አወጣጥ በምዕራፍ ሁለት የተገለጸውን የድህረ ማዳመጥ መልምጃዎች አላማ ከማሳካት ረገድ የተሻለ ቢሆንም በቅድመ ማዳመጥ እና በማዳመጥ ጊዜ መልመጃዎች አቀራረብ ላይ ክፍተት አለ ፡፡ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ፣ እንዲሁም ተማሪዎች ምንባቡን የሚያዳምጡበትን ምክንያት ተረድተው በትኩረት እንዲያዳምጡ ፣ ተማሪዎች ከርዕሱ ወይም ከቀረቡ መረጃ መሳሪያዎችን መሰረት በማድረግ ለሚቀርብላቸውን መረጃ ጉጉት እንዲያድርባቸው ማዳረግ የሚችሉ መልመጃዎች መሆን አለባቸው፡ ሆኖም 90% የሚሆኑት የቅድመ ማዳመጥ መልመጃዎች ትኩረት የቀደመ እውቀትን መቀስቀስ ስለሆነና ሌሎች ብልሀቶች ትኩረት ስላልተሰጣቸው የቅድመ ማዳመጥ መልመጃዎች ከሚቀርቡበት አላማ አንጻር ድክመት ይታይበታል፡፡ የማዳመጥ ሂደት መልመጃዎች አላማ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ምንባብ በጥልቀት እንዲያዳምጡ ማስቻልና ተፈላጊ መረጃዎችን ለይቶ ማውጣትን ማስቻል ነው ፡፡ስለዚህ በዚህ ወቅት መቅረብ ያለባቸው ጥያቄዎች አብዛኛው ተማሪ ሊመልሳቸው የሚችላቸው ፣ የአዳምጦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚያስችሉ መሆን እንደለባቸው ምሁራን ይገልጻሉ ፡፡ ይሁን እንጂ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ማዳመጥን ለማስተማር ከተዘጋጁት ምንባቦች የወጡት አብዛኛዎቹ መልመጃዎች መመሪያቸው ከቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው ፡፡

መምህራን የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ስለሚረዱ ምንባቦችና ከምንባብ የወጡ መልመጃዎች ያላቸውን ግንዛቤ ለሚፈተሽ በተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ፤ ስለ ምንባቦቹ አዘገጃጀት የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ሲሆን ስለመልመጃዎቹ ያላቸው ግንዛቤ ግን በክፍል ምልከታ እንደታየው አነስተኛ ነው ፡፡

ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች አስፈላጊ ማስተማሪያ መሳሪዎችን ይዘው መገኘታቸውን በተመለከተ ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ዝቅተኛ ነው፡በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው የማዳመጥ ትምህርቶች በምንባብ መልክ ሲዘጋጁ ስዕሎች፣ ካታዎች…የማስተማሪ መሳሪያ በመሆን ያገለግላሉ ፡፡ ሆኖም ለጥናት ለተመረጠው የክፍል ደረጃ ማዳመጥን ለማስተማር የተዘገጁ ምንባቦች በመረጃ መሳሪያዎች ተደግፈው የቀረቡ አይደሉም፡

በአጠቃለይ ከላይ በተገለጹት የጥናቱን ንዑሳን አላማ መሰረት ያደረጉ የጥናት ውጤቶች መሰረት የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ፣በመምህሩ መምሪያ የቀረቡት ምንባቦችና በመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጁት መልመጃዎች አቀራረብ ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው አመቺነት አነስተኛ ነው፡

## 5.2 አስተያየት

በዚህ ክፍል የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ማዳመጥ ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦችና መልመጃዎች አቀራረብ ዙሪያ እንደችግር ለተነሱ ሀሳቦች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግብአት ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ አስተያየቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች**፡ - የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች ከተማሪዎቹ የዕለት ከዕለት ገጠመኝ ጋር ያላቸው ትስስር አነስተኛ ነው፤ ምንባቡን ተጨባጭ ሊያደርጉ የሚችሉ ስዕላዊ መግለጫዎች ቢካተቱም ከቀረበው ምንባብ ጋር የሀሳብ ልዩነት አለው ፤ ለአንብቦ መረዳት ከቀረቡ ምንባቦች ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ስላላቸው መደጋገማቸው ሳቢነታቸውን ቀንሶታል እንዲሁም ከምንባብ የወጡት መልመጃዎች የቀረቡበትን አላማ ከግብ ከማድረስ አንጻር ውስንነት ታይቶባቸዋል ፤ እንዲሁም የተመደበው ጊዜ በቂ አይደለም ፡፡ ስለሆነም የመጽሐፍ አዘጋጆች ፡ -

- ✓ የተጠቀሱትን ክፍተቶች በመመልከት ወደፊት መጽሐፍቶች ሲዘጋጁ የተጠቀስትን ጉድለቶች ሞልተው ማቅረብ ቢችሉ፣

**ለመምህራን** ፡ - የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው መምህራን የተዘጋጁ ምንባቦችን በማጠቀም ማዳመጥን ለማስተማር የሚያስችል እቅድ እንደማያቅዱ ፣ በመጽሐፉ ከቀረቡት መልመጃዎች ውጪ ተማሪዎችን ለማዳመጥ የሚያነሳሱ መልመጃዎችን አሰቀድሞ የማዘገጀት ውስንነት አለባቸው፡ ስለሆነም መምህራን ፡ -

- ✓ ማዳመጥን ለማስተማር ማዘጋጀት የሚያስችል እቅድ አቅደው ማስተማር ቢችሉ፣
- ✓ በመጽሐፉ ላይ ብቻ ከመወሰን ተማሪዎችን ለማዳመጥ የሚያነሳሱ ሜልመጃዎችን አዘጋጅተው ለተማሪዎች ቢያቀርቡ፣

**በተማሳሳይ የጥናት ማስክ ጥናት ለሚያካሄዱ አጥኚዎች ፡-**ጥናቱ የተካሄደው የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ማዳመጥን ለማስተማር በመምህሩ መምሪያ የተዘጋጁ ምንባቦችና ከምንባቡ የወጡ ሜልመጃዎች ክህሎቱን ለማስተማር ያላቸው አመቺነት ሚፈተሸ ብቻ ነው ፡፡ ይህም የሆነው አጥኚዋ ካለባት የገንዘብና የጊዜ እጥረት የተነሳ ነው ፡፡ የጥናት ውጤቱ ለትናት ለተሚረጠው የክፍል ደረጃ የተዘጋጁ ምንባቦችና ከምንባብ የወጡ ሜልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር ምቹ እንዳልሆኑ ያማላክታል ፡፡ በሚሆኑም በቀጣይ ጥናት የሚያደርጉ አካላት፡ -

- ✓ ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦችና ሜልመጃዎች ለማስተማር ምቹ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች ካሉ ማግምም ቢችሉ
- ✓ ለሌሎች የክፍል ደረጃዎች ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁ ምንባቦችና ከምንባብ የወጡ ሜልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር ያላቸውን አመቺነት ቢፈትሹ ተገቢ እንደሆነ የጥናቱ አቅራቢ ታማላክታለች፡፡

## ዋቢዎች

ማነፍን ደፈረሱ ፡፡ (2000) ፡፡ “የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረበ

ማልመጃዎችን ይዘትና አዘገጃጀት ግምገማ በ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ ትምህርት ሞርሀ ግብር ፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፡፡ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነዘዴ ፣ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

ሚረው አለሙ፡ (1998) ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996) ፡፡ በስነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር ፡፡ አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ቶማስ ዳኛቸው፡ (2002) ፡፡ "የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን የማዳመጥ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ፍተሻ

በኦሮሚያ ክልል በተሚረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት "፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ ትምህርት ሞርሀ ግብር ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋን የማስተማር ስነዘዴ፣ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡(ያልታተመ)

አልማዝ አለማየሁ፡፡ (2006) ፡፡"በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶችና

ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ፣በሶስት የአዲስ አበባ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ናሙነት"፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ ሞርሀ ግብር ፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋ የማስተማር ስነዘዴ ፣ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

እቴነሽ ተገኝ ፡፡ (1986) ፡፡"በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ሞርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል

ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ ትምህርት ሞርሀ ግብር ፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋን በማስተማር ስነ ዘዴ፣ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

Anderson, A. and Lynch, J (1988).Listing: Oxford university press.

------------- (1991) . Listening .Oxford : Oxford University press.

Brown, G. {1987}. Twinty –Five Years of teaching Listing Comprehension English Teaching Forum.

Colliet,T.and Stephen, S. (1987). Literature in the language classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Cuningworth, A. (1989). Evaluating and selecting EFLT Teaching Material: Oxford: Heinemann.

Grant, N. (1989). the Most of Your Text Book. New York: Longman Group.

----------- (1987). Making the most of your text Book. London: Longman.

Harmer, J. (2001). The practies of English language Teaching . New York: Longman Group Ltd.

Haozhang,X (1997).Tape Recorders,Role-plays,and Turn-take in large ELF Listening and speaking classes.English Teaching Form.

Kral,T.(1996).Teacher Development Making The Right Moves.Washington D.C.English language program Division.

Littlewood.W.(1981) .Communative Language Teaching. CombridgeUniversity Press.

McDonough,J. and shaw,C. (1994).Materials and Methods in ELT . Oxford Black Well.

Nunan ,D.(2001). Second language Acquision.The Cambridge Guide to teaching.

Rixon. A .(1986). Developing Listing Skill .London: Macmillan Publishers. Ltd.

------------(1990). Teaching Listing .New York : Longman .Ink.

Underwood ,M. (1989). Teaching Listing . London : Longman Group Ltd.

-------------,Mary.(1994).Teaching Listening.NewYork:Longman,Inc.

Ur,penny (2002).A course in language Teaching .cambridje :Cambridge University Press.

Williams, David. (1984). Developing Criteria for Text Book Evaluation ELT Journal Vol.3.

Yagang.F.(1993).Listening Problems and solutions.English Teaching Forum.

# አባሪዎች

አባሪ. ሀ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ ፣የቋንቋዎች ጥናት ፣ጆርናሊዝምና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ-ግብር

በአዲስ አበባ ከተማ ማስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በ2017 ዓ/ም በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላስ የጽሁፍ ማጠይቅ፡ -

ውድ መምህርት/ር

የዚህ ማጠይቅ ዋና አላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተዘጋጅቶ የስምንተኛ የክፍል ተማሪዎችን ማዳመጥ ለማስተማር፣ በመምህሩ መምሪያ የቀረቡ ምንባቦችና በመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጁ ከምንባቦቹ የወጡ ሜልመጃዎች ክህሎቱን ለማስተማር ያላቸው አመቺነት ምን እንደሚመስል ከመምህራን መረጃ ማሰብሰብ ነው፡ ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ የሚቀርብሎትን ጥያቄዎች በማስተዋል በማንበብ ገንቢ የሆነ አስተያየትዎን ይሰጡኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ክፍል አንድ ፡ - አጠቃላይ መረጃ

ጾታ ------------------ዕድሜ ---------------

የአገልግሎት ዘመን -----------------አመታት

የትምህርት ደረጃ -------------------------

የተመረቁበት የትምህርት አይነት ------------------------

ክፍል ሁለት ፡ -ማጠይቆች

መመሪያ አንድ ፡ -ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመመዘኛ ማስፈርቶቹ ላይ በተቀመጡት መግለጫዎች አማካኝነት ተገቢ ነው የሚሉትን ሜልስ የ X ን ምልክት በማስቀመጥ ያሜልክቱ ፡፡

የፍረጃ ደረጃዎች

በጣም እስማማለሁ ----1 እስማማለሁ--2 አልስማማም ----3

ፈጽሞአልስማማም------4

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የማዳመጥ ክሒልን ለማስተማር በመማሀሩ መምሪያ የቀረቡት ምንባቦች የማዳመጥ ፍላጎትን የሚያነሳሱ ናቸው፡ | | | | |
| 2 | በመማሀሩ መምሪያ የቀረቡት ምንባቦች በበቂ ሁኔታ ማዘጋጀታቸው | | | | |
| 3 | የማዳመጥ ክሂል ምንባቦቹ ለትምሀርት ደረጃው ያላቸው ተስማሚነት | | | | |
| 4 | የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት ምንባቦች ከተማሪዎች ማሀበራዊ ሀይወት ጋር ያላቸው ቅርበት | | | | |
| 5 | ምንባቦቹ ከተማሪዎቾ ፍላጎትና ዳራዊ እውቀት ጋር ያላቸው ተዛምዶ | | | | |
| 6 | የምንባቦቹ የአቀራረብ ሳቢነት | | | | |
| 7 | ከምንባብ የወጡት መልመጃዎች በቂነትና ተገቢነት | | | | |
| 8 | ተማሪዎች ለማስተማሪያነት በቀረቡት ምንባቦችን የማዳመጥና መልመጃዎቹን የማስራት ተነሳሽነታቸው | | | | |
| 9 | ክሀሎቱን ለማስተማር የተመደበው (የተሰጠው ጊዜ ) ከይዘቱ ጋር ያለው ተስማሚነት | | | | |
| 10 | የማዳመጥን ክሂል ለማስተማር የተዘጋጁት ምንባቦች (ጽሁፎች)የቀረቡበት ቋንቋ ከተማሪዎች የቋንቋ ችሎታና የትምሀርት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ ነው | | | | |
| 11 | በመማሀሩ መምሪያ የቀረቡት ምንባቦች አዳዲስ ሚረጃዎችን መያዛቸው | | | | |
| 12 | በመማሀሩ መምሪያ የቀረቡት ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጁ ጽሁፎች መልመጃዎችን ለማሰራት አመቺ ናቸው | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 13 | ማዳመጥን ለማስተማር ስነ-ጽሁፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ተካተዋል | | | | |
| 14 | በማስተማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የገሀዱን አለም እውነታ የሚያንጸባርቁ ጽሁፎች ማዳመጥን ለማስተማር ቀርበዋል | | | | |
| 15 | ምንባቦቹና ከምንባቡ የወጡት መልመጃዎች የትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ አስተዋጽኦ አላቸው | | | | |
| 16 | ክህሎቱን ለማስተማሪያ የቀረቡት ምንባቦች በቂ ስዕላዊ መግለጫን ይዘዋል | | | | |

17 በመምህሩ መምሪያ የቀረቡት ምንባቦች ክህሎቱን ለማዳበር ያላቸው አመቺነት ምን ይመስላል

የማዳመጥ ክሂል ምንባቦች ለክፍል ደረጃው ተስማሚ ናቸው?

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,::

18 አዳምጦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር በቀረቡት ምንባቦችና ከምንባብ በወጡ መልመጃዎች ክህሎቱን ለማስተማር ያለዎት ተነሳሽነት ምን ይመስላል? ለምን?

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,::

19 የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የሚዘጋጁ ምንባቦችና ከምንባብ የወጡ ሚልመጃዎች አቀራረብ እንዴት መሆን እንዳለበት ያሎት ግንዛቤ ምን ይመስላል?

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,፡፡

20 አዳምጦ የሚረዳት ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙት የአቀራረብ ስልት ምን ይመስላል(ምንባቡን የሚያስደምጧቸው እንዴት ነው) ? በተማሪዎቹ ላይ ያለውስ ለውጥ ?,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,፡፡

21 በመምህሩ መምሪያ በቀረቡት ምንባቦችና በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ በተዘጋጁት ከምንባብ በወጡ ሚልመጃዎች አዳምጦ የሚረዳትን ክሂልን ለማስተማር የሚያስቸግሩ ነገሮች አሉ? ----------------
----------------------------------------------------------------
----------------------

ሚልስዎት አዎ ከሆነ ችግሮቹ ምንድናቸው? ለችግሮቹስ ምን አይነት መፍትሄ መውሰድ ያስፈልጋል?

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,
,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,, ,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,፡፡

ለማጠይቁ ምላሽ በማስጠት ላደረጉልኝ ትብብር ምስጋናዬ የላቀ ነው፡ ፡

አባሪ . ለ

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት የአዳምጦ መረዳት ምንባቦችና ከምንባብ የወጡ መልመጃዎች አቀራረብ ምልከታ ማከናወኛ ቅጽ

አጠቃላይ መረጃ

ምልከታ ቁጥር -------------------

ቀን -----------ወር--------------ዓ/ም -------------

የትምህርት ቤቱ ስም -------------------

ትምህርቱ የተጀመረበት ጊዜ -------------------

ሴክሽን ------------------ ክፍለ ጊዜ --------------

የተማሪ ብዛት ------------------

የእለቱ ትምህርት ርዕስ -----------------------

ለትምህርቱ የተመደበለት የጊዜ ርዝማኔ ------------------

የእለቱ ትምህርት አላማዎች

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

መመሪያ፡ -በዝርዝር የቀረቡትን ሐሳቦች በተዘረዘሩት አማራጮች የክንውን ደረጃዎች ስር እንደክንውኑ ሁኔታ የ<< X >> ምልክት በማጠቀም ይሞላል፡፡

| ተ.ቁ | የምልከታ ማካታተያ ነጥቦች | በጣም ከፍተኛ | ከፍተና | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለክፍለ ጊዜው የማዳመጥ ምንባብ ክህሎቱን ለማስተማር ያለው እገዛ | | | | |
| 2 | የእለቱን ትምህርት በተማለከተ በቂ ዝግጅት ስለመደረጉ | | | | |
| 3 | የእለቱን ትምህርት በተማለከተ እለታዊ እቅድ ስለማዘጋጀቱ | | | | |
| 4 | ተማሪዎች ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበው መንባብ ለማዳመጥ ፍላጎት እንዲያድርባቸው የሚያስችሉ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በአግባቡ መቅረባቸው | | | | |
| 5 | ተማሪዎች እየተነበበላቸው ያለውን ምንባብ በአግባቡ እየተከታተሉ መሆኑን ለማወቅ የሚቀርቡ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች በአግባቡ መቅረባቸው | | | | |
| 6 | ተማሪዎች አዳምጠው የተረዱትን ለመማለስ የሚያስችሉ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች መቅረባቸው | | | | |
| 7 | የእለቱ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎች እንዴት ማዳመጥ እንዳለባቸው | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ግልጽ የሆነ መመሪያ የማስጠት ሁኔታ | | | | |
| 8 | ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ከተማሪዎቹ ማህበራዊ ህይወት ጋር ተዛምዶ ተጨባጭ በሆነ ሜልኩ መቅረቡ | | | | |
| 9 | ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጀው ምንባብ ሲቀርብ ተማሪዎች ዋናዋና ነጥቦችን ማስታወሻ እየያዙ የሚከታተላቸው ሁኔታ | | | | |
| 10 | የማዳመጥ ትምህርቱን ለማስተማር የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ማጠቀማቸው | | | | |
| 11 | ተማሪዎች የማዳመጥ ምንባቡ በሚነበብላቸው ወቅት ያልተረዷቸውን ቃላትና ሀረጋት መዝግበው ከመምህራቸው ጋር የመወያየታቸው ሁኔታ | | | | |
| 12 | በቅድመ ማዳመጥ ፣በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ ወቅት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የተማሪዎች የተሳትፎ ሁኔታ | | | | |
| 13 | ክህሎቱን ለማስተማር የተደበው ጊዜ በቂ የሚሆኑ ሁኔታ | | | | |
| 14 | የቅድመ ማዳመጥ ፣የማዳመጥ ሂደትና የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች አላማ ለተማሪዎች ማገሩ | | | | |
| 15 | ክህሎቱን ለማስተማር የነበረው ተነሳሽነት | | | | |
| 16 | ማዳመጥን ለማስተማር የተመደበው ጊዜ በቂ ስለሚሆኑ | | | | |
| 17 | ተማሪዎች እየተነበበላቸው ላለው ጽሁፍ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ይሰጡት የነበረው ትኩረት | | | | |